## << <<ማሳሰቢያ>> >>

### በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

<<የተወደዳችሁ የልዑል እግዚአብሔር ቤተ ሰቦች፥
የቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ወዳጆች ሁላችሁም>>

የጥንታዊው ታሪክና የሥልጣኔ ዋና ምንጭ የሆነችው ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ከጥንት ጀምራ እምነቷ እንዲስፋፋና እንዲጠናከር፣

የእምነቷ ተከታዮች ሕዝበ ክርስቲያንም በሥጋዊውም ሆነ በመንፈሳዊው ትምህርትና ዕውቀት እየተኰተኰቱ፣ እንዲያድጉና በመልካም ስነ ምግባር እንዲኰለብቱ ከፍተኛውን ጥረት ስታደርግ ኖራለች።

አሁንም የእምነቷ ተከታይ ሕዝበ ክርስቲያን ሁሉ መንፈሳዊውንና ሀገራዊውን ታሪኩ ከመሠረቱ በማወቅ ሃይማኖቱን፣ ሥርዓቱንና ባህሉን እንዲጠብቅ፣ በሰላም፣ በፍቅርና በአንድነት ሆኖ እየተረዳዳ እንዲኖር በመጻሕፍትም ሆነ በአባቶች፣ በካህናትና በምሁራን ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አማካይነት እያስተማረች፣ እየመከረች ትገኛለች።

ተከታዮቿም ከጊዜ ወደ ጊዜ በዕውቀት እየበለፀጉ፣ በጥበብና በአመለካከት እያደጉ፣ በቊጥርም እየበዙ በመሔድ ላይ እንደሆኑ ግልጽ ነው።

ይሁን እንጂ አብዛኛው ኅብረተሰብ፥ በተለይም በውጭ ሀገር የሚገኘው ወጣቱ ትውልድ የራሱን እምነት፣ ታሪኩን፣ ቋንቋውንና ባህሉን እንዳያውቅ የሚኖርበት አካባቢና ሁኔታው ሁሉ ተፅዕኖ

ይኸውም ቅዱሳን ሐዋርያት ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀጥታ ተረክበው ያስተላለፉልን የክርስትና እምነትና ሥርዓቱ ሁሉ በሐዋርያት ተከታዮች አርድእትና ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አባቶቻችን እየተመራ ትክክለኛውን ትምህርቱንና ሃይማኖታዊ ሥርዓቱን፥ እንዲሁም መንፈሳዊ ባህሉንም ጠብቆ በአንድ መሥመር እየሔደ እንደሚገኝ ይታወቃል።

(ሙሉውን ዝርዝሩ በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ ምዕራፍ 16፥ በገጽ 153 እና 157 ይመልከቱ)

እኛ እያንዳንዳችን የክርስቶስ ወገኖች እውነተኞች ሕዝበ ክርስቲያን ነን የምንለውም ከዚህ በላይ ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው በትክክለኛው እምነታችን በመጽናት፣ በቀደምት አበውና በቅዱሳን ሐዋርያት አማካይነት ከጌታችን የተሰጠንን፣ በቅዱሳት መጻሕፍትና በሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አባቶቻችን በትውፊት (በቅብብሎሽ) የተረከብነውን ሃይማኖታችንን፣ ምንም ሳንበርዝና ከሌላውም ጋር ሳንቀላቅል፣ ጥንታዊውንና ታሪካዊ ሥርዓቱን በመጠበቅ መልካም ምግባር ሠናይ ሥራ በሚባለው በጾም፣ በጸሎት፣ በርኅራኄ፣ በምጽዋት፣ በትሕትና፣ በሰላምና በእውነተኛ ፍቅር አንድ በመሆን በመንፈሳዊ ባህላችን ስለምንገልጸው ነው።

ትክክለኛ የሃይማኖት ትርጉምና ሃይማኖትን ከመልካም ምግባር ጋር መያዝ፣ ሃይማኖታዊ ሥርዓትንም መጠበቅ ማለት ደግሞ ይህ እንደሆነ እውነትን ለሚቀበል ሁሉ ግልጽ ነው።

ቅዱሳን አባቶቻችን ብራና ፍቀው፣ ቀለም አውጥተው፣ ብዕር ቀርፀው፣ ጥሬ እየቆረጠሙ፣ ውሃ እየጠጡ፣ በሱባኤ ተወስነው ጽፈው ያስተላለፉልን ምንም ያልተቀላቀለበቱ፣ ያልተበረዘውና ያልተከለሰው፣ ቋንቋው ግእዝ የሆነ፥ በተቀደሱ መንፈሳውያን መነናትና የታሪክ ሥፍራዎች የሚገኝ ትክክለኛውን ሃይማኖታችንንና ሥርዓቱን ሁሉ ለዘለዓለም እየነገረን የሚኖር ቅዱስ መጽሐፋችን ትርጉሙና ምሥጢሩ ለመናፍቃን በቀላሉ ሊገባቸው ስለማይችልና በየጊዜው የሚለዋወጠውን የስሕተት ጉዟአቸውንም ስለማይደግፍላቸው ለማደናገሪያ የሚያመቹዋቸውን አንድ አንድ ጽሑፎች አዘጋጅተው እያባዙ የማሰናከያ ምዕራፍንና ቍጥርን ብቻ ቍነፅለው እየያዙ በመቅረብ የዋሁን ሕዝብ ለማደናገር ይሞክሩ ይሆናል።

ሆኖም ግን ቅዱስ መጽሐፍን፣ ጥሬ ንባቡን፣ ትርጉሙንና መሠረታዊ ምሥጢሩንም ጠንቅቆ በሚያውቅ ላይ ሊራመዱ አይችሉም።





ቅዱስ መጽሐፍን በመልካም ምግባር የሚተረጉም እውነተኛ ክርስቲያንንም ከቶ አያታልሉም።

ይኸውም እውነተኛ ክርስቲያን ቅዱስ መጽሐፍን በወረቀት ብቻ ሳይሆን በተግባርም ጭምር ነውና የሚያነበው ምሥጢሩንም በሥራ ነው የሚተረጉመው።

በሉቃስ ወንጌል 10፥38፤ እንደተዘገበው፥ እንደዚሁም በትርጓሜ ቅዳሴ ማርያም <<በግእዙ>> <<ናጥሪ እንከ አርምሞ ወትዕግሥተ ከመ ማርያም እኅተ ማርታ>> እንደ ማርያም እኅተ ማርታ አርምሞንና ትዕግሥትን ገንዘብ እናድርግ ከሚለው ቀጥሎ ያለውንም ታሪክ እንደምንመለከተው፥ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዘመነ ሥጋዌው ማርታና ማርያም የተባሉትን ሁለት እኅት (እትማማቾች) ለመንፈሳዊ ተግባር ሲያሠማራ አንዷን (ማርታን) በረድእነት (በሥራ ላይ) መድቦ፥ ሌላኛዋን (ማርያምን) ደግሞ ለትምህርት እንዳዘጋጀ ሁሉ፥ የእግዚአብሔር አገልጋዮችና እውነተኞች ክርስቲያኖችም እግዚአብሔር በፈቀደላቸው መሠረት፥ በገዳም ይሁን በደብር፥ በሱባኤ ተወስነው ወይም በበረኻ ወድቀው ወይም ደግሞ ማንም ተራ ሰው መስለው በመካከላችን እየተገኙ ስለ ሰው ስርየተ ኃጢአት፣ ስለ ዓለም ሁሉ ሰላምና ደኅንነት የሚጸልዩ አሉ።

ወንበር ተክለው፣ ጉባኤ አስፍተውም ሆነ በተለያየ ሥፍራ እየተዘዋወሩ ምንም ያልተቀላቀለበትን፣ ያልተበረዘውንና ያልተከለሰውን እውነተኛውን የክርስቶስ ቃል ንባቡን፣ ትርጉሙንና ምሥጢሩን ጠንቅቀው በመማር የሚያስተምሩም አሉ።

እንደየችሎታቸው በልዩ ልዩ ደረጃ ተመድበው መንፈሳዊውን አገልግሎት የሚሰጡም አሉ።

በልዩ ልዩ ሥራ ላይ ተሠማርተው በጉልበታቸው ሠርተው አብያተ ክርስቲያናትን የሚያሠሩ፣ አስፈላጊ የሆነውን ንዋየ ቅድሳት (የማመስገኛ ንብረት) ሁሉ እያሟሉ ቤተ ክርስቲያን እንድትኖር የሚያደርጉ፣ የቤተ ክርስቲያኒቱን አባቶች፣ ሊቃውንቷንና አገልጋዮቿ ካህናትን የሚንከባከቡ፣ የተቸገሩትንም ሁሉ ባላቸው ዓቅም የሚረዱም አሉ።

ክርስቲያናዊ ግዴታቸውን በተግባር የሚወጡ፣ ቅዱስ መጽሐፍን በመልካም ሥራ የሚተረጉሙ፣ ሃይማኖትን ከመልካም ምግባር ጋር የያዙ፣ ሃይማኖታዊ ሥርዓታቸውንና መንፈሳዊ ታሪካቸውን የጠበቁ እውነተኞች ሕዝበ ክርስቲያን የሚባሉ እነዚህ ናቸው።

አዎ ሃይማኖታቸውን በመልካም ሥራ ገልጸዋል፣ ሃይማኖታዊ ሥርዓታቸውንና መንፈሳዊ ታሪካቸውንም ጠብቀዋል ሊባሉ የሚችሉ ይህን ያደረጉ ሰዎች ናቸው።

ታዲያ እነዚህ ይመሰገናሉ እንጂ ማንም ሊነቅፋቸው አይገባም።

ስለሆነም እውነተኛ ሕዝበ ክርስቲያን፣ የክርስቶስ ወገን ነኝ የሚል ሁሉ እንደ እነዚህ የእግዚአብሔር ወዳጆች በመሆን መልካሙን የጽድቅ ሥራ መሥራት ይገባዋል።

ሆኖም ግን እንደዚህ አሁን እንደተጠቀሰው ያለውን መልካም ሥራ መሥራት ተገቢ መሆኑ እየታወቀ እውነትን ወደ ጎን እየተው፣ ያልሆነውንም ሆነ እያሉ የሚያደናግሩ፣ ሃይማኖታዊ ሥርዓታችንና ጥንታዊ ታሪካችን እያቃለሉ አፈጻጸሙን የሚለዋውጡ፥ መንፈሳዊውና ሀገራዊው አንድነታችንን የሚለያዩ እንደበታቸው የክፋት ምላጭ የሆነ፣ መሠረታዊ እውቀትና በእውነት ላይ የተመሠረተ ልባዊ ትሕትና የሌላቸው፣ በተለያየ ምክንያት የሚደራጁ ቡድኖችም ሊኖሩ እንደሚችሉ በመገመት በሰላማዊት፣ የተዋሕዶ ቅድስት ቤተ ክርስትያናችንና በሕዝበ ክርስቲያኗ መካከል አለመግባባትና ቅሬታ እንዳይኖር አስቀድመን በማሰብ ጥንቃቄን ማድረግ፥ ስለ እምነታችንና መሠረታዊ ሥርዓቱ ሁሉ ግልፅ ያልሆነልን ካለ ሳንቸኩል፥ ልባዊና እውነተኛ በሆነ መንፈሳዊ ትሕትና ከአበውና ከምሁራን ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ልሳን (አንደበት) በተገቢው መንገድ መማር፣ መጠየቅ፣ መረዳትና ማስረዳት ይገባናል እንጂ አንድ አንድ ነገሮች በተከሠቱ ቍጥር <u><<ሆ>></u> ማለትና መጨበጫ በሌለበት አሉባልታ መነዳት አደገኛ በመሆኑ ሃይማኖታዊ ሥራችን ሊሆን አይገባውም።

መንፈሳዊ ባህላችንም አይደለም፣ ሕጋዊ ተግባራችንም ሊሆን አይችልም።

የሃይማኖት ምሥጢር ቀላል አለመሆኑን መገንዘብ አለብን፣ ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን (ከሥርዓተ ሃይማኖት) ውጭ እንዳንሆንም ማስተዋል ያስፈልጋል።

ምክንያቱም ለሁሉ ሥርዓት አለውና በትዕግሥት መወያየት፣ በእውነተኛ ፍቅር መጠያየቅ፣ በትሕትና መተራረም ቀዳሚ ተግባራችን ሊሆን ይገባል።

<u>ሙሉ ምሥጢሩን በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ ምዕራፍ 21 በገጽ 183 እና 184 እንመልከት።</u>





<u>እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፥</u>

<<ኩለንታኪ ሠናይት እንተ እምኅቤየ አልብኪ ነውር ወኢምንትኒ ላዕሌኪ>>

(ወዳጄ ሆይ ሁለንተናሽ ውብ ነው፥ ነውርም የለብሽም)
<u>መሐልየ (መኃልየ) ሰሎሞን 3 (4) ፥7</u>

<u>አስቀድሞ በአምላክ ኅሊና ታስባ የኖረች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፥</u> ለአምላክ እናትነት የተመረጠችው ገና ሳትወለድ ሲሆን፥ ከእናቷ ማኅፀን ሳለች ጀምራ መንፈስ ቅዱስ ከነውርና ከውርስ ኃጢአት ሁሉ የጠበቃት ፍጽምት፣ ንጽሕት፥ ቅድስትና ቡርክት ናት።

በሊቃውንት አባቶቻችን ጉባኤ ተብሎ የማያውቅ በዘመናችን አንድ አንድ ሰዎች ጥንተ አብሶ እያሉ የሚጠሩትም አሳገኛትም፣ ፈጽሞም የለባትም።

አዎ ሰማይን ያለ ምሰሶ ያቆመ፣ ምድርንም ያለ መሠረት ያፀና፥ እነአብርሃምን፣ እነኤርምያስንና እነዳዊትን ገና ሳይወለዱ ከእናታቸው ማኅፀን ሳሉ ጀምሮ ለመልካም ሥራ ያዘጋጀ እግዚአብሔር፥ ሁሉን ማድረግ ስለሚችል፥ ለእርሱ እንዳችም የሚሳነው ነገር የለምና እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ከተመረጡት የተመረጠች፣ ከከበሩት የከበረች ልዩ፣ ንጽሕት፣ ቅድስትና ቡርክት አድርጎ ፈጥሯታል።
<u>መዝ 21፥1, 57፥3, 135፥5, ኤር 1፥4፥ማቴ 1፥18</u>
ይህን እውነት እየተቃወሙ ከዚህ ውጭ በሆነ መንገድ የሚንቀሳቀሱ ካሉ የእግዚአብሔርን ከሃሊነትንና የባሕርይ አምላክነትን እየተቃወሙ እንደሆኑ፥ ማለትም እግዚአብሔርን ሁሉን ማድረግ አይችልም በማለት ላይ እንዳሉ በመረዳት ከስሕተታቸው ተመልሰው ንስሓ ሊገቡ ይገባቸዋል።

ምክንያቱም ይህን ያደረገ እግዚአብሔር ስለ ሆነ እግዚአብሔር ለእመቤታችንም ሆነ ለሌሎች ቅዱሳን የሰጠውን የማይሻር የአማላጅነት፣ የረድኤት፣ የበረከትና የምሕረት ቃለ ኪዳንን (ቃል ኪዳንን) እንደናቁ፣ የእግዚአብሔርን ዘለዓለማዊ ስጦታ እንዳቃለሉ፣ በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ አማላጅነት፣ ፍጹም ቅድስና እና ፍጹም ንጽሕና ላይ እንደቀለዱ፥ በአጠቃላይ በማቴዎስ ወንጌል ያለውን ሰማይ ከምድር ጋር

ዘእንበለ ህላዌ፥ ኢህልዎ፣ አልቦ፣ ኢምንት ማለት፥

አለመኖር፣ ከፅንስ በፊት በምንም ተገልጾ ያለመታየት፣ አለመፀነስ፣ አለመወለድ ሲሆን፥

ህላዌ፣፥ ሀልዎ፣ እምጎበ አልቦ ጎበ ቦ፣ ምንት ግን፥

መኖር፣ መፀነስ፣ መወለድ፣ ከእናት ኾድ ወደ ብርሃን መውጣት፣ መገኘት፣ ተገልጾ መታየት ነው።

ልደት የሚለው ዘርና ዋና ግንዱ <<ወለደ>> ከሚል የግዕዝ ግስ ስለሚወጣ በዐቢይ አንቀጹ ወለደ በማለት ልደት ብሎ ይገኛል።

# ምዕራፍ <<2>>

ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልደትና መሠረታዊም ሥጢሩ፥

<<ሀ>> ከጌታችን ልደት በፊት የነበረው ሁኔታና የመወለዱ ዋና ምክንያት፥

<<ለ>> ከልደቱ በፊት የተነገሩት ትንቢታት፥

<<ሐ>> የመልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ብሥራትና ምሥጢሩ፥

<<መ>> የልደቱ ፍጻሜና ምሥጢሩ፥

<<ሠ>> እኛ ልናደርገው የሚገባን፥

<<ረ>> የጌታችን ዘመነ ልደት በቅደም ተከተል ሲተነተን የሚሉት ከዚህ ቀጥለው በየክፍላቸው ይብራራሉ።

## ክፍል<<1>>

## <<ሀ>> ከጌታችን ልደት በፊት የነበረው ሁኔታና የመወለዱ ዋና ምክንያት፥





በኦሪት ዘፍጥረት ከምዕራፍ 1 ጀምሮ በተከታታይ ምዕራፎች እንደምንመለከተው ልዑል እግዚአብሔር ፍጥረቱን ሁሉ ሲፈጥር ሰውን በአርአያውና በምሳሌው ፈጥሮ ከሁሉም ፍጥረት አልቆ አክብሮ በገነት አኑሮት ነበር። ዘፍጥረት 1፥26 2፥7።

ከዚህም ጋር ሕግንና መመሪያን ሰጥቶ ሕጉን እንዲያከብር አዞት ነበር።

አዎ ይህን ዕፀ በለስ የበላህ እንደሆነ የኃጢአትን ሞት ትሞታለህና ዕፀ በለስን አትብላ ብሎታል።

ይኸውም የፈጣሪና የፍጡር መለያ፥ የአዛዥና የተአዛዥ ልዩ ምልክት መሆኑ ነው። በፈጣሪና በፍጡር መካከል ሕግና መመሪያ መኖሩንም የሚያስገነዝብ ነው። ዘፍጥ 2፥16።

ይሁን እንጂ ሰው (አዳም) የፈጣሪውን ሕግና መመሪያን ጠብቆ በተፈቀደለት መሠረት መኖር ሲገባው የፈጣሪውን ሕግና መመሪያ ጥሶ፣ የታዘዘውን አፍርሶ ያልታዘዘውን ሲፈጽም፣ በልቡ አስቦ ያልተፈቀደለትን ያውም ከዐቅሙ በላይ የሆነውን የባሕርይ አምላክነትን ሲሻ (ሲፈልግ) በመገኘቱ ከፈጣሪው ጋር ተጣልቶ ከገነት ወጥቶ ከክብር ወደ ሐሣር ተለውጦ መርገም ወድቆበት ከሕይወት ወደ ሞት ተባረረ። ዘፍጥ 3፥1።

በመሆኑም በአዳምና በሔዋን ላይ የወደቀው መርገም ባለመነሣቱ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የነበረው 5500 ዘመን ሁሉ፥ መርገሙን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ በመስቀል ተሰቅሎ እስከ ደመሰሰው ድረስ የመርገም፣ የፍዳ፣ የጨለማ፣ የችግርና የጭንቀት ዘመን ስለ ሆነ ሰው መልካምም ይሥራ ክፉ ኑሮው በሲኦል በችግር ውስጥ ነበር ማለት ነው።

ነገር ግን በፍጥረቱ የማይጨክን የርኅራኄና የጽድቅ ባለቤት ልዑል እግዚአብሔር በአምስት ቀን ተኩል (ከመንፈቅ) ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ ብሎ ለአዳም በሰጠው አምላካዊ ተስፋ መሠረት ትንቢት ተነግሮ ሱባኤ ተቆጥሮ ካበቃ፥ ጊዜው ሲደርስ፥ ማለትም በነቢያቱ አንደበት ትንቢትን አናግሮ ከጨረሰ በኋላ 5500 ዓመተ ዓለም ሲፈጸም ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ።

ዘመኑም አምስት ቀን ያለው አምስት ሺህ ዓመት ሲሆን፥ እኩለ ቀን (መንፈቀ ዕለት) ያለው ደግሞ አምስት መቶ ዓመት ነው።

<u>በሌሎች ነቢያትም ብዙ ምሳሌና ትንቢት ተነግሯል።</u>

በተለይም <<በምሥጢር አፍላቂነቱና በአስደናቂ ትንቢቱ ልበ አምላክ>> (የአምላክ ልብ) እየተባለ የሚጠራው፣ አምላካዊ ሥራን ከመሆኑ በፊት በመዝሙሩ አስተካክሉ የሚናገር፥

ስለ ጌታችንና ስለ እመቤታችን መሠረታዊ ምሥጢር አስቀድሞ የተገለጸለት ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት በመዝሙሩ በየክፍሉ ትንቢቱንና ምሳሌውን ደጋግሞ አመሥጥሮታል።

<u>ለምሳሌም፥</u>

<u>1ኛ በግእዙ፥</u>

ኖላዊሆሙ ለእስራኤል አፅምዕ፥
ዘይርእዮሙ ከመ አባግዓ ዮሴፍ፥
ዘይነብር ላዕለ ኪርቤል አስተርእየ።

<u>ቀጥተኛ ትርጉሙ፥</u>

የእስራኤል ጠባቂ ሆይ አድምጥ፤
ወይም ደግሞ በትርጓሜው ተስተካክሉ ሲገለጥ፥
እስራኤልን እንደ ዮሴፍ በጎች የምትመራ፣ በኪሩቤል ላይ
የምትቀመጥ ተገለጥ ይላል። <u>መዝሙረ ዳዊት 79፥1።</u>

<u>በመሠረታዊ ትርጓሜው ምሥጢሩ ሲተነተንም፥</u>

እስራኤል ዘነፍስን የምትጠብቅ አምላካችን ሆይ አድምጥ፤
በረድኤት ተገለጥ፥ ሥልጣንህንና ረድኤትህን በሥጋ ገልፀህ፣
ሰው ሆነህ ተወልደህ አድነን፤

አቤቱ ከሲኦል ወደ ገነት መልሰን፣ ከገነትምም ወደ መንግሥተ ሰማያት አግባን ማለት ነው።

<u>2ኛ ግእዙ፥</u>

ምስሌከ ቀዳማዊ በዕለተ ኃይል፥
በብርሃናተሙ ለቅዱሳን፥
ወለድኩከ እምከርሥ እምቅድመ ኮከበ ጽባሕ።

<u>ቀጥተኛ ትርጉሙ፥</u>





ከአንተ ጋር ቀድሞ በኃይልህ ቀን በቅዱሳን ብርሃን ከአጥቢያ ኮከብ አስቀድሞ ከሆድ ወለድኩህ ይላል።

(ከጥንተ ፍጥረት በፊት ከአንተ ጋር ነበርሁ፣ ከመላእክት መፈጠር በፊት ወለድኩህ ሲል ነው) <u>መዝሙረ ዳዊት 109፥3</u>

<u>ይህ መዝሙር</u>፥ አንድነቱን ሲገልፅ በፍጥረት ጊዜ ከአንተ ጋር ነበርኩ፣ ቅድመ ዓለም ያለ እናት መወለዱን ሲገልፅም ዓለም ሳይፈጠር አስቀድሞ እካል ዘእምአካል ባሕርይ ዘእምባሕርይ ወለድኩህ የሚል ሲሆን፥ ድኅረ ዓለም ያለ አባት ያለ ዘርዐ ብእሲ ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለዱን ሲገልጽ ደግሞ የነቢያት ትንቢት በተፈጸመበት፥ መላእክት <<ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ >> ብለው ባመሰገኑበት ቀን ወለድኩህ የሚል ምሥጢር ይገኝበታል።

<u>በውስጡ</u> የአንድነትንና የሦስትነትን ምሥጢር የያዘ እንደመሆኑ መጠንም፥ የእግዚአብሔር አንድነትንና ሦስትነትን በሰፊው ያመሠጥራል።

አዎ ጌታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በመወለዱ በመላእክትና በልሳነ ሰብእ (በሰው አንደበት) በፍጥረቱም ሁሉ እግዚአብሔር አብ፣ እግዚአብሔር ወልድ፣ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ተብሉ ተመሰገነ፥ <u>አብ ወላዲ፣ ወልድ ተወላዲ፣ መንፈስ ቅዱስ ሠራጺ እንደሆነም በፍጥረቱ በግልፅ ታወቀ።</u>

የእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት ምንም እንኳ ቀድሞም በነቢያት አንደበት ሲነገር፣ በብሉያት ቅዱሳት መጻሕፍትም ሲመሠጠር እንደነበረ ቢታመንም በልደቱ ምሥጢር ደግሞ በሥራ ተገለጠ፣ ጎልቶ ታየ።

ከዚህ ቀጥሎም በሐዲሳት ቅዱሳት መጻሕፍት ተጻፈ፤ በጉባኤም በትርጓሜ ተመሠጠረ፤ በሥፋት ለሁሉ ተነገረ ማለት ነው።

<u>ስለሆነም</u> ጌታችን በቤተ ልሔም በተወለደ ጊዜ ሰማያት ተከፍተዋል።

መላእክትም <<ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ>> እያሉ እግዚአብሔርን ለማመስገን ከሰማይ ጌታችን ወደ ተወለደባት ወደቤተ ልሔም ሲወርዱ፣ ከምድርም ወደ ሰማይ ሲወጡ ስለነበር ትንቢት በተፈጸመበት መላእክት ባመሰገኑበት ቀን ወለድኩህ ይላል።

## ክፍል <<3>>

## <<ሐ>> የመልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ብሥራትና ምሥጢሩ፥

<<ወበሳድስ ወርኀ ተፈነወ ገብርኤል መልአክ>> ሉቃስ 1፥26።

አዎ በሉቃስ ወንጌል 1፥26 ጀምሮ እንደምንረዳው መልአከ ብሥራት ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል፥ የእግዚአብሔር አገልጋይ የሆነው ካህን አሪት ዘካርያስን ወደሚያገለግልበት ቤተ መቅደስ ሔዶ፥ ዘካርያስ ሆይ ጸሎትህ ከእግዚአብሔር ፊት ደርሷል፤ መካን የምትባለው ኤልሳቤጥ ሚስትህም ወንድ ልጅን ትወልድልሃለች ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ።

ይኸውም ፍጹም ደስታ ማለት ነው ብሎ ካበሠረው በኋላ፥ በስድስተኛው ወሩ ናዝሬት ገሊላ ወደ ነበረችው ወደ ቅድስት ድንግል (ማርያም) ከእግዚአብሔር ተላከ።

የድንግሊቱም ስም ማርያም ነበረ መልአኩም ወደ እርሷ ገብቶ <<ደስ ይበልሽ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው፤ አንቺ ከሴቶች ተለይተ የተባረክሽ ነሽ>> አላት።

አዎ ምሥጢሩ በትርጓሜው መሠረት ሲብራራም፥ እግዚአብሔር ከሥጋሽ ሥጋን፤ ከነፍስሽም ነፍስን ነሥቶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ይሆናልና (ከአንቺ ይወለዳልና) በነቢያት ትንቢት በመላእክት ተልእኮ ደስ ያለሽ ምልዕተ ክብር ሆይ (ተፈሥሒ) ደስ ይበልሽ ማለት ነው።

ይህ <<በአበው ትርጓሜ መሠረት ሲብራራ>>

ከሴቶች መካከል፥ ማለትም ከሁሉም ሴቶች ተለይተሽ አንቺ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለብሽ፤ በረከተ ሥጋን በረከተ ነፍስን ከልጅሽ ከኢየሱስ ክርስቶስ እያማለድሽ የምታሰጪ ነሽ፤

የማኅፀንሽ ፍሬ ኢየሱስ ክርስቶስም መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለበት፤ በረከተ ሥጋን በረከተ ነፍስን የሚያድል ወይም የሚሰጥ ነው የሚል ምሥጢር ይገኝበታል።





ይኸውም፥ <<ከሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አባቶቻችን መደበኛ የጉባኤ ትርጓሜና ከቅዱሳት መጻሕፍት ትክክለኛ ምሥጢር እንደምንገነዘበው>>

ከሴቶች መካከል ተለይተሽ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለብሽ ነሽ ብሎ በአዳምና በሔዋን ላይ የወደቀው ከፈጣሪያቸው እንዲርቁ የሚያደርግ መርገም፥ በተለይም ደግሞ በሔዋን ላይ የነበረው ፃዕረ ወሊድና አስቸጋሪ የሆነ ሥጋዊ ጠባይዕ (ሥጋዊ ሐሳብም ሆነ ሥጋዊ ባሕርይ) ሁሉ በእመቤታችን ላይ ግን እንደሌለ፥ (እንደዘመናችን አነጋገር ጥንተ አብሶ የሚባለውም እንዳላገኛት፤ ፈጽሞም እንደሌለባት)

በረከተ ሥጋን በረከተ ነፍስን እያማለድሽ የምታሰጪ ነሽ ብሎም አማላጅነቷን በሚገባ ያስረዳናል።

እዎ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር ስለሌለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ገና ሳትወለድ ከእናቷ ማኅፀን ሳለች ከማንኛውም ነውርና የውርስ ኃጢአት ጠብቆ፥ ከሌሎች ንጹሓን የተለየች ንጽሕት፤ ፍጽምት፥ ሆና እንድትወለድ አድርጓታል።

መዝ 131፥13, ኤር 1፥4፥

የአሊታ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መጽሐፈ ሰዋስውንም ከመቅደሙ፥ ክፍል 3፥ ገጽ 25 እንመልከት።

ይህ በፍጡር ሊለካ የማይቻል የማይመረመር የእግዚአብሔር አምላካዊ ጥበብና አምላካዊ ሥራ ነው።

ሌላ ፍጡር ሁሉ ምንም እንኳ ኃጢአትን ከመሥራት የታቀበ ከገቢር ንጹሕ ቢሆንም፥ ከተፈጥሯዊ ኀልዮ (ሓሳብ) ፈጽሞ ንጹሕ ሊሆን አይችልም እመቤታችን ግን ከኀልዮም፤ ከገቢርም፥ ማለትም ከማሰብም ሆነ በተግባር ከመፈጸም ሁሉ ንጽሕት፤ ፍጽምት ናት።

እንደዚሁም ደግሞ፥ <<የማኅፀንሽ ፍሬ የተባረከ ነው የተባለው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ>> ሁሉ በእጁ የሆነ፤ ሰጭ የሚያድል፤ ተማላጅ (የሚለመን) እንጂ አማላጅ እንዳልሆነ ከዚሁ ምሥጢርም በሚገባ መረዳት እንችላለን።

ድንግል ማርያምም ከሐዲስ ንግግሩና እንግዳ ከመሆኑ የተነሣ ለጊዜው ደንግጣ እንደነበር ቅዱስ መጽሐፋችን ይናገራል።

አዎ ድንግል ማርያም መልአኩ ባበሠራት ጊዜ፥

ሊቁ ኢትዮጵያዊ ቅዱስ ያሬድ በግእዝ ቋንቋ፥ <<እምአይቴ ዘመጽአ ዝ እንግዳ ዘይዜንወኒ ፍ/ሥሓ>> በማለት በጣዕመ ዜማው እንዳመሠጠረው፥ (የመጋቢት በዐለ እግዚአብሔር ድጓ)

ይህ ደስታን የሚነግረኝ ዕንግዳ ከየት የመጣ ነው? ቀድሞ አባቴ አዳምንና እናቴ ሔዋንን ያታለለ ያ ጥንተ ጠላታችን ሰይጣን ይሆን? ወይስ እውነት መልአከ እግዚአብሔር ነው? ብላ ነበር ማለት ነው።

ፍርሃትን ማስወገድ ልማዱ የሆነው መልአክ ብ/ሥራት ቅዱስ ገብርኤልም በእግዚአብሔር ፊት ጸጋን (ባለሟልነትን) አግኝተሻልና አትፍሪ አላት።

እያይዞም እነሆ ትፀንሻለሽ፤ ወንድ ልጅንም ትወልጃለሽ፤ ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ። እርሱ ታላቅ ነው፤ የልዑል ልጅም ይባላል፤ ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊት ዙፋን ይሰጠዋል፤ በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘለዓለም ይነግሣል፤ ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም አላት።

መሠረታዊ ትርጉሙ <<እነሆ ትፀንሻለሽ፤ ወንድ ልጅንም ትወልጃለሽ>> ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ፤ እርሱ ዐቢይ ነው።

የልዑል እግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅ ነው፤ በያዕቆብ ቤት ለዘለዓለም ይነግሣል፤ ለመንግሥቱም <<ለባሕርይ አምላክነቱ>> ኅልፈት ሽረት የለውም ማለት ነው። ዳን 7፥13, ሉቃ 1፥31, ዕብ. 1፥1 ጀምሮ በሰፊው እንመልከት።

ማርያምም ወንድን ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል አለችው።

አዎ ቅድስት ማርያም ግን በኀሊናም በሥጋም ማለትም በሐሳብም ሆነ በግብር ድንግል፤ ንጽሕት፤ ፍጽምት ናትና እኔ እንኳንስ የገቢር የኀልዮም የለብኝም፤ ይህ የምትለው ነገር እንዴት ሊሆን ይችላል።





ለመሆኑ መሬት ያለዘር ስታበቅል ሴት ያለውንድ ስትፀንስ የት አየህና ነው እንደዚህ የምትለኝ ብላ መለሰችለት ማለት ነው።

መልአኩም መንፈስ ቅዱስ ወደ አንቺ ይመጣል፤ በአንቺ ላይ ያድራል፤ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል፥

ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል አላት።

አዎ መልአኩ፥ መንፈስ ቅዱስ ወደ አንቺ ይመጣል፤ በአንቺ ላይም ያድራል፤ ኃይለ ልዑል ወልድም ይፀልልሻል፥

ማለትም ሥጋሽን ይለብሳል፤ ከአንቺ ይወለዳል።

ከአንቺ የሚወለደውም ተራ ፍጡር፥ (ዕሩቅ ብእሲ) ሳይሆን <<ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ>> ተብለው ከሚመሰገኑት ከሦስቱ አካላት፥

(ከሥላሴ) አንዱ አካል እግዚአብሔር ወልድ ነው፥

ከአንቺ የሚወለደው ሁሉን የፈጠረ፤ የፍጥረታት ባለቤት የሆነ እግዚአብሔር አምላክ ነው አላት።

እያይዞም መልአኩ እነሆ መካን ትባል የነበረችው ኤልሳቤጥ ዘመድሽ እንኳ ከአረጀች በኋላ ወንድ ልጅን ፀንሳለች ይኸውም ስድስት ወር ሆኖታል።

ስለዚህ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና ይህ የምነግርሽ ሁሉ ይሆናል አላት።

ቅድስት ድንግል ማርያምም እንደቃልህ ይሁንልኝ ይደረግልኝ አለችው።

ከዚህ በኋላ አምላክ ከሥጋዋ ሥጋን፤ ከነፍሷም ነፍስን ነሥቶ (ተዋሕዶ) ሰው ሆነ፤ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ ማለት ነው።

ማቴ 1፡1,ዮሐ 1፥1, 1ኛ የዮሐንስ መልእክት 5፥1። በሰፊው እንመልከት

አዎ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም።

## ክፍል <<4>>

## <<መ>> <<የልደቱ ምሥጢርና ፍጻሜው>>

### የልደቱ ምሥጢር እንዴት እንደነበረ ሲተነተንም÷

በሉቃስ ወንጌል ም 2÷1 ጀምሮ እንደምንረዳው ሰው ሁሉ በየሀገሩ ከግብር ገብቶ ይቆጠር ዘንድ÷ ማለትም ዛሬም የሕዝብ ቆጠራ እንደሚደረገው መላው ሕዝብ በየአከባቢው እየተገኘ እንዲቆጠር፣ እንዲመዘገብ በዘመኑ ከነበረው ገዥ ከአውግስጦስ ቄሣር ትእዛዝ ወጣ።

በመሆኑም የዳዊት ወገን የሆነው ዮሴፍም ከድንግል ማርያም ጋር በመሆን እንዲጻፍ (እንዲመዘገብ) ከናዝሬት ከገሊላ የዳዊት ሀገር ወደምትሆን ወደ ይሁዳ ወደ ቤተ ልሔም ሔደ ይላል ቅዱስ መጽሐፉ።

በነገራችን ላይ ይህች ቤተ ልሔም የምትባል ቦታ÷ ቀደም ሲል ትንቢት የተነገረላት ናት።

ይኸውም የቅዱስ መጽሐፋችን ታሪክ እንደሚያስረዳን÷ ሚክያስ የተባለ ነቢየ እግዚአብሔር በሌላው ክፍል ሲያስተምር ውሎ ወደ ማታ አካባቢ በቤተ ልሔም በኩል ሲያልፍ <<ቤተ ልሔምን>> ተፈታ ወይም ጠፍ ቦታ፣ ዑና ሆና ቋያ በቅሉባት እንዳያትና÷

አዝኖ ተክዞ አንቺ የኤፍራታ ዕጣ የምትሆኚ <<ቤተ ልሔም>> የይሁዳ ነገሥታት ከነገሡባቸው ሀገሮች ብትበልጪ እንጂ ከቶ አታንሽም÷

እንዲህ ጠፍ እንደሆንሽ አትቀሪም።

ንጉሥ ይነግሥብሻል፣ እስራኤል ደጅ ይጠኑብሻል፣ ነጋሪት ይሰማብሻል፣ ድንኳን ይተከልብሻል፣ አሕዛብም ግብርን ይገብሩብሻል ብሎ÷ አስቀድሞ ትንቢት ተናግሮባት

እንደ ነበር ይታወቃል። ሚክ 5÷2, ማቴ 2÷6።

ትንቢቱ አልቀረም ሆኗል፣ ሁሉም ተፈጽሞአል።





ለጊዜው ዘሩባቤል ነግሦባታል፣ ነጋሪት ተሰምቶባታል፣ ድንኳን ተተክሎባታል፣ እስራኤል ደጅ ጠንተውባታል አሕዛብም ገብረውባታል።

ዋናው ትንቢቱና ፍጻሜው ደግሞ÷ ለኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሆነ ጌታችን በተወለደ ጊዜ የብርሃን ድንኳን ተተክሎባታል፣ እስራኤል ዘነፍስን የሚጠብቅ ጌታ ተወልዶባታል።

አዎ ጌታችን በቤተ ልሔም በተወለደ ጊዜ ቤተ ልሔም የመላእክት ምስጋና ተሰምቶባታል፣ ነገደ መላእክት ደጅ ጠንተውባታል÷ ሰብአ ሰገልም ወርቅን፣ ዕጣንንና ከርቤን ገብረውባታል።

በመዝሙረ ዳዊት መዝ 71÷10። እንደምንረዳው ጌታችን በእርሷ በቤተ ልሔም በተወለደ ጊዜ ሰብአ ሰገል ወርቅን÷ ዕጣንንና ከርቤን አምጥተውለታል ለማለት ነው።

የዚህ ምሥጢር ወደፊት በዝርዝር ይብራራል።

እንዲሁም ይህ ሁሉ በርሷም ላይ ስለተፈጸመ ምሳሌው ለድንግል ማርያምም ይሆናል።

ወደዋናው ርእሳችን እንመለስና ዮሴፍና ቅድስት ድንግል ማርያም ወደ ዳዊት ሀገር ወደ ይሁዳ ቤተ ልሔም በወጡበት ጊዜ ድንግል ማርያም ጌታን ፀንሳ ስለነበር የምትወልድበት ሰዓት ደረሰ።

የሚያድሩበትንም ሥፍራ ባለማግኘታቸው ድንግል ማርያም ጌታችንን በጎል (በበረት) እንደ ወለደችው።

ወቅቱም ብርድ በመሆኑ በጎል (በበረቱ) የነበሩ እንስሳት ሕፃኑ ጌታን በእስትንፋሳቸው እንደ አሟሟቁት ቅዱስ መጽሐፋችን ያስረዳናል።

እናቱ ድንግል ማርያምም ለዚህ የታደሉ÷ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ በኋላ በሚቀብሩት ጊዜ በድርብ በፍታ ገንዘው እንደሚቀብሩት÷

ካህናትም ዕለት ዕለት (በየዕለቱ) በቅዳሴ ጊዜ ሥጋውን በማጎፈድ (በጨርቅ) እንደሚጠቀልሉት አስቀድሞ ተገልጾላት በማጎፈድ (በጨርቅ) ጠቀለለችው አውራ ጣቱንም አሠረችው ይላል።

በዚያች ሀገር መንጋቸውን ተግተው የሚጠብቁ ዕረኞችም ስለ ነበሩ የእግዚአብሔር መልአክ መጥቶ በአጠገባቸው ቆመ።

ከቤተ ልሔም ጀምሮ እነርሱ እስከ አሉበት ድረስም ብርሃን ፈሰሰላቸው። (ልዩ የሆነ ብርሃን እንደ ውሃ ፍስስ ብሎ በራ ማለት ነው)

<u>እነርሱም</u> እጅግ እንደ ደነገጡ+ እንደ ፈሩና መልአኩ ግን ሁል ጊዜ ዳንኤል አትፍራ፣ ዘካርያስ አትፍራ፣ ማርያም አትፍሪ እያለ ፍርሃትን እያስወገደ፣ እያረጋጋ መናገር፣ ማብሠርም ልማዱ ስለሆነ <u>እነዚህ ዕረኞችንም</u> አይዟችሁ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታን፣ የምሥራችን እነግራችኋለሁና አትፍሩ።

ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት+ እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና እንዳላቸው ቅዱስ መጽሐፋችን እየነገረን ይገኛል።

<u>ይኸውም በመሠረታዊ ምሥጢሩ ሲብራራ የእግዚአብሔር መልአክ</u> መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለበት በረከተ ሥጋን በረከተ ነፍስን የሚያድል፤ የዓለም መድኃኒት የሚሆን የባሕርይ አምላክ ክርስቶስ+ በዳዊት ባሕርይ፣ በዳዊት ከተማ ተወልዷልና እናንተንም ሌላውንም ሰውን ሁሉ ደስ የሚያሰኝ ዜናን፣ ትልቅ ደስታን እነግራችኋለሁ።

ምልክቱ ሕፃኑን አውራ ጣቱን ታሥሮ በኀል፥ ማለትም በበረት ተጥሎ (ተኝቶ) በጨርቅ ተጠቅልሎ ታገኙታላችሁ አላቸው ማለት ነው። <u>ሉቃስ 2፥10</u>

ይህን ሲናገርም ብዙ የሰማይ ሠራዊት ወይም የሰማይ መላእክት+

<<ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ>> እያሉ ከመልአኩ ጋራ ድንገት ነጕደው ሲመጡ ተሰሙ።

<u>አዎ ጌታችን በተወለደ ጊዜ፥</u> መላእክት ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰው በጎ ፈቃዱ በማለት እግዚአብሔርን አመስግነዋል።

<u>መሠረታዊ ትርጉሙ፥</u> አምላክ ፍጹም ሰው ቢሆን ሥጋ አምላክ ሆኖአልና+ ፍጹም ሰው ለሆነ አምላክ ምስጋና ይገባዋል፣





እግዚአብሔር ለሰው ግእዛኑን (ነፃነቱን) ይሰጠው ዘንድ ከድንግል ማርያም ስለ ተወለደ።

በምድር ዕርቅ ተወጠነ፣ (ተጀመረ) በዓለም ሰላም ሠፈነ፣ በአዳም ትውልድ ሁሉ አንድነት ሆነ ማለት ነው።

<u>ዋናው ምሥጢሩም፥</u> አምላክ ሥጋን በመዋሐዱ (ሥጋን በመልበሱ) ፍጹም ሰው ሆኖ ከቅድስት ድንግል ማርያም በመወለዱ፥ ፍጹም ተዋሕዶውን ለመግለጽ ነው።

<u><<ዮም አሐደ መርዔተ ኮኑ መላእክት ወሰብእ ከመ ይሰብሕዎ ለክርስቶስ በቃለ አሚን>> ይላል በግእዙ፥</u>

<u><<ይህ ከአበው ትርጓሜ የተጠቀሰ ሲሆን ቅዱስ ያሬድም በድጓው በጣዕመ ዜማው አመሥጥሮታል>></u>

ይኸውም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተ ልሔም በተወለደ ጊዜ፥ ሰውና መላእክት በአንድ ማኅበር ሆነው+ ማለትም መላእክት ከኖሎት ጋራ፣ ኖሎትም ከመላእክት ጋራ በኅብረት በመሆን እግዚአብሔርን አመስግነዋል ማለት ነው። <u>ሉቃስ 2፥14</u>

እኛም ያንን መሠረት በማድረግ ዛሬ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በአንድነት ሆነን እናመሰግነዋለን።

በጌታችን ልደት ጊዜ+ ከዚህ ከፍ ብለው የተጠቀሱት ሰብአ ሰገል እየተባሉ የሚጠሩትም ለጌታችን ወርቅን፣ ዕጣንንና ከርቤን አቅርበውለታል።

<u>የሰብአ ሰገል ስጦታዎች በዝርዝር ሲብራሩ፥</u>

ከቅዱሳት መጻሕፍትና ከሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አባቶቻችን እንደምንረዳው፥ ሰብአ ሰገል በማለት የምንጠራቸው የሰገል ሰዎች አምላክ እንደ ሆነ ለማጠየቅ ዕጣንን አመጡለት፣ ንጉሥ እንደሆነ ለማጠየቅም ወርቅን አመጡለት፣ እንደዚሁም ማኅየዊ የሚሆን የሞቱ ምሳሌ ከርቤን አመጡለት ይላል። እነዚህ በሰብአ ሰገል የቀረቡ ስጦታዎች አምላካዊ ሥራዎችን የሚያመለክቱ ዐበይት ምሥጢራት አሉዋቸው።

ይኸውም ለምሳሌ ያህል ከመሠረታዊ ምሥጢሩ በዐጭሩ ብንጠቅስ፥

## ወርቅ አመጡለት ይላል፥

የወርቅ ጥራት በእሳት ተረጋግጦ ይህ ንጹሕ ወርቅ ነው እንደሚባል፥ ጌታም ንጹሐ ባሕርይ በመሆኑ በዚህ ለማመሳሰል ሲሆን፥

በጌታችን አምነው እንደ ወርቅ በእሳት መከራ ተፈትነው ፈተናውን አልፈው ሰይጣንና የሰይጣንን ሥራዎች ሁሉ አሸንፈው የሚገኙ ምእመናንም (ሰዎችም) ሃይማኖታቸውና ምግባራቸው እንደወርቅ የነጠረ፣ የጠራ (ንጹሕ) እንደሆነ ለማመልከት ነው።

## ዕጣንን አመጡለት ይላል፥

ዕጣን መልካም መዓዛ አለው ጌታችንንም ምዑዘ ባሕርይ ነህ ለማለት ሲሆን፥ እንዲሁም ዕጣን በተስፋ ይመሰላል፥ ዕጣን ከሩቅ እንደሚሸት ተስፋም ያላዩትን እንዳዩት፣ ያልያዙትን እንደያዙት፣ (እንደጨበጡት) ታደርጋለች ወይም ታስመስላለች፥

ወደ ፊት ተስፋው መልካም የሆነ ሰው በፊቱ ይታወቃል፥ ፊቱ ደስተኛ ነው፣ አእምሮውም ሁሉ ብሩህ ነው።

ጌታችንም ተስፋ ላጡት ሁሉ ተስፋ፣ ፍጹም ደስታ፣ ፍጹም ሕይወት ስለ ሆነ በዚህ ለመግለጽ ነው።

## ከርቤን አመጡለት ይላል፥

ከርቤም በአንድነት፥ በሰላምና በፍቅር ይመሰላል።

ከርቤ የተሰበረውን ይጠግናል፣ የተለያየውንም አንድ ያደርጋል።

ጌታችንም ከማኅበረ መላእክት የተለየውን አዳምን ወደ ቀደመ ክብሩ መልሶ ከማኅበረ መላእክት እንደሚጨምረው፥ የተለያየውንም ሁሉ በማዋሐድ፥ ለፍጥረቱ እውነተኛውን ፍቅር ሰጥቶ፣ መላውን ዓለም ሰላም እንደሚያደርግ ለማመልከት ነው። መዝ 71፥10።እንመልከት።

<<ምሥጢሩ በአበው ትርጓሜ መሠረት ሲብራራ ነው>>





አዎ አስቀድመው የተገለጹ ምሳሌዎችና ምልክቶች በጌታችን አምላካዊ ሥራዎች በተለያየ ጊዜ በተግባር ላይ ታይተዋል፣ በየክፍሉና በየደረጃውም ተፈጽመዋል።

እነዚህ የፍጹም ሕይወት፥ የአንድነት፥ የሰላም፥ የዕርቅና የፍቅር ምሳሌዎችና ምልክቶች ሲሆኑ፥ በውስጣቸው እኛም በኅብረት፣ በእውነተኛው ፍቅር አንድ ሆነን ፈጣሪያችን እግዚአብሔርን ማመስገን እንደሚገባን የሚያስገነዝበን መልካም አርአያና ትምህርት ያለበት መልእክት አለ።

## በተጨማሪም ከዚህ በታች ያሉትን የአማርኛ ጥቅሶች እንመልከታቸው፥

1ኛ እግዚአብሔር ጽዮንን (እመቤታችንን) ይህች ለዘለዓለ <<ማደሪያዬ>> (ማረፊያዬ) ናት ብሎ መርጧታል። መዝ 131፥13 (132፥13)

2ኛ ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም፣ ሰውም አይገባበትም፣ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር <<ገብቶበታልና>> ተዘግቶ ይኖራል። ሕዝ 44፥2

ይህ ቃል አምላክን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና የወለደች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም፥ አምላክን ከመፅነስዋ በፊት፣ አምላክን በፀነሰች ጊዜ፣ በምትወልድበትም ሆነ ከወለደችው በኋላ ድንግል፣ ፍጽምት፣ ንጽሕት መሆኗን እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ያደረበት ነቢዩ ሕዝቅኤል አስቀድሞ በዓይነ ኅሊና የተመለከተ፣ በምሥጢረ ትንቢትም የተናገረ እንደሆነ ነው የሚያስረዳን።

3ኛ በስድተኛውም ወር መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ወደ አንዲት <<ድንግል>> (ማርያም) ከእግዚአብሔር ዘንድ ተላከ። ሉቃ 1፥26።

ቃሉ መልአከ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ ቅድስት ድንግል ማርያም በተላከ ጊዜም እመቤታችን ነውርና ኃጢአት የሌለባት፥ ድንግል፣ ፍጽምት፣ ንጽሕት መሆኗን ነው የሚያረጋግጥልን።

ሰላምታ፣ የጸጋና የክብር ስግደት እንደሚገባትም ከዚሁ መረዳት እንችላለን። ሉቃ 1፥28

## ክፍል <<5>>

## እኛ ልናደርገው የሚገባን፥

### <<ሠ>> 5ኛ የልደቱ መሠረታዊ ምሥጢር

ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ሲሆን፥

ቀጥሎ ደግሞ የልደቱን ምሥጢር መሠረት እያደረ ከልዩ ልዩ ቅዱሳት መጻሕፍት እየጠቀሰና እያብራራ እኛ ልናደርገው የሚገባንን የሚያስገነዝብ መልእክት ይሆናል።

ይኸውም፥

<<በ1ኛው የዮሐንስ መልእክት ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅምና እርስ በእርሳችን እንዋደድ በእርሱም በኩል በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና በዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ዘንድ ተገለጠ>> ተብሎ እንደተነገረን ጌታችን የተወለደው ለእኛ ፍጹም ሕይወት መሆኑን በመረዳት ቃሉን ሰምተን በተግባር ላይ ልናውል፣ በእውነተኛው ፍቅር አንድ በመሆን ፈጣሪአችን እግዚአብሔርን ልናመሰግን ይገባናል። 1ኛ ዮሐ 4፥7። እንመልከት።

አዎ አሁንም በዚሁ መልእክት በምዕ 5፥1 ጀምሮ <<ክርስቶስ ነው ብሎ በኢየሱስ የሚያምን ሁሉ ከእግዚአብሔር ተወልዷል፣ ወላጁንም የሚወድ ሁሉ ከርሱ የተወለደውን ይወዳል፣

እግዚአብሔርን ስንወድ ትእዛዛቱንም ስናደርግ የእግዚአብሔርን ልጆች እንድንወድ በዚሁ እናውቃለን፣ ትእዛዝቱንም ልንጠብቅ የእግዚአብሔር ፍቅር ይህ ነውና፣ ትእዛዛቱም ከባዶች አይደሉም ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋልና ዓለምንም የሚያሸንፈው እምነታችን ነው>> ተብሎ እንደተነገረን፥

በእምነታችን ጸንተን፣ ሃይማኖታችንን በመልካም ምግባር፣ በሠናይ ሥራ እያነጽን፥ በሰላም፣ በፍቅርና በርኅራኄ እየተረዳዳን፣ በቅዱ ቃሉ መሠረት መንፈሳዊውን ባህላችን በመጠበቅ በሕገ እግዚአብሔር፣ በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያናችን እየተመራን መኖር አለብን ማለት ነው።





እንደዚህ ሆነን የተገኘን እንደሆን አሁንም ከዚሁ መልእክት ሳንወጣ ማለትም በ1ኛ የዮሐንስ መልእክት ምዕራፍ 3፥1 ጀምሮ የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደሰጠን እዩ ተብሎ እንደተገለጸልን የእግዚአብሔር ልጆች ልንባል እንችላለን። መንገዳችን ከዚህ ውጭ ከሆነ ግን በጨለማ ጎዳና እየተጓዝን ነን ማለት ነው የጨለማ መንገድ ደግሞ ወደ ገደል ነው የሚወስድ።

በመሆኑም በዮሐንስ ወንጌል <<ብርሃን በጨለማ ይበራል ጨለማውም አላሸነፈውም>> ተብሎ እንደተመሠጠረው ብርሃን ሕይወት እግዚአብሔር አምላካችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ፣ በእውነተኛው መንገድ ሆኖ እየበራልን ነውና የጨለማውን ጎዳና ትተን በትክክለኛው የብርሃን መሥመር ወደ እግዚአብሔር፥ ወደ ዘለዓለማዊ ሰፍራችን፣ ወደ መንግሥተ ሰማያት ልንጓዝ ይገባናል። የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 1፥4።

አዎ ራሱ ጌታችን በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ስምንት ቍጥር አሥራ ሁለትም፥ <<እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም>> ብሏልና በእውነተኛው ብርሃን በኢየሱስ ክርስቶስ መንገድ የሚጓዝ ሁሉ ወደ ጨለማ አይሔድም። ዮሐ 8፥12።
አሁንም በዚሁ ወንጌል፥ <<ብርሃን ከእናንተ ጋር ነው የብርሃን ልጆች እንድትሆኑ በብርሃኑ እመኑ፣ ጨለማም እንዳይደርስባችሁ ብርሃን ሳለላችሁ በብርሃን ተመላለሱ>> በማለት በቅን ልቡና ከብራነው እግዚአብሔር አምላካችን ምን ጊዜም ከእኛ ጋር ስለሆነ በእርሱ ብርሃንነት እንድንመላለስ አስረድቶናል። ዮሐ 12፥35።

ስለዚህ በጽድቅ፣ በእውነተኛ መንገድ ወደ እውነተኛው ብርሃናችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወታችን፣ ወደ መንግሥተ ሰማያት መመላለስ ይገባናል ማለት ነው።

ቅዱስ ጳውሎስም በሮሜ ምዕራፍ 13፥11 መልእክቱ <<ከዕንቅልፍ የምትነሡበት ሰዓት አሁን እንደደረሰ ዘመኑን ዕወቁ>> በማለት እንደነገረን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሊያድነን ስለ መጣ፣ ምሕረትንና ሰላምን ለማስፈን ከቅድስት ድንግል ማርያም ስለ ተወለደ፣ ከልደቱ በፊት የነበረው መርገምና ፍዳ ተደምስሶ፣ ኀዘኑ ችግሩ ጭንቀቱ ሁሉ አልፎ፣ ጨለማው ተገፎ፣ እውነተኛው የሕይወት ብርሃን መጥቷልና፥

ሊቀ ኢትዮጵያዊ ቅዱስ ያሬድም በድጓው÷
<<ብርሃነ ሕይወት ዘኢይጸልም>> ያለው

(ከቊስቋም ኅዳር 6 ቀን እስመ ለዓለም የተጠቀሰ ነው)

ጊዜያት የማይፈራረቁት፣ ጨለማ የማያሸንፈው፣ የማይጠፋ የሕይወት ብርሃን ኢየሱስ ክርስቶስ በርቶልናልና
<<ንዑ ናንሶሱ በብርሃኑ>>

ኑ ሁላችንም በክርስቶስ በብርሃን እንመላለስ ይለናል ቅዱስ ቃሉ።

ቅዱስ ጳውሎስም በኤፌ 5÷14 መልእክቱ <<አንተ የምትተኛ ንቃ ከሙታንም ተነሣ (ተነሥ) ክርስቶስም ያበራልሃል>> ብሎ እንደገለጸው ነቃ ብለን እውነተኛው የማይጠፋ ብርሃን ወደሚበራበት፣ ፍጹም መድኃኒት ወደሚገኝበት ወደ ዘለዓለማዊ መኖሪያችን ወደ እግዚአብሔር ቤት ብንገሠግስ መልካም ነው።

አዎ ከላይ ከፍ ብሎ እንደተነገረን ከእንቅልፋችን የምንነቃበት ዘመን አሁን ነውና በእንቅልፍ ከሚመሰለው ካለማወቅ ወደማወቅ፣ ከኃጢአት ተግባር ወደ ጽድቅ ሥራ መሻገር ያስፈልገናል። ከእንቅልፋችን ነቃ ብለን ቅዱስ ቃሉን ልንመለከተው፣ ልብ ብለንም ልናስተውለው÷ የሚነገረን ያለው ለሁላችንም ለእያንዳንዳችን መሆኑን በሚገባ ልንረዳው ይገባናል።

ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ÷ <<ከእርሱ ጋር ኅብረት አለን ብንል በጨለማም ብንመላለስ እንዋሻለን እውነትንም አናደርግም። ነገር ግን እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን ብንመላለስ ለእያንዳንዳችን ኅብረት አለን፣ የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ደምም ከኃጢአታችን ያነጻናል። ኃጢአት የለብንም ብንልም ራሳችንን እናስታለን፣ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም>> በማለት እንደነገረን እያንዳንዳችን ቃሉን በተግባር ላይ ማዋል ይጠበቅብናል።

በደለኞች መሆናችንን አምነን ፈጣሪአችን ይቅር እንዲለን በንስሐ ወደ እርሱ መቅረብ ይገባናል ማለት ነው።

በ1ኛ የዮሐንስ መልእክት እንደተገለጸልን እግዚአብሔር ፍጹም ብርሃን ስለሆነ ጨለማ በእርሱ ዘንድ ከቶ የለምና ከእርሱ ጋር ኅብረት አለን የምንል ከሆነ የጨለማውን ተግባር ሁሉ መጣል÷





ክፋትን፣ ተንኮልን፣ ቅንዓትን፣ ምቀኝነትን፣ ቂምንና በቀልን መተው ቀዳሚ ተግባራችን ሊሆን ይገባል። 1ኛ ዮሐ 1÷5 ጀምሮ።

በተጨማሪም ቅዱስ ጳውሎስ<<ቀድሞ ጨለማ ነበራችሁና አሁን ግን በጌታ ብርሃን ናችሁ። የብርሃኑ ፍሬ በበጎነትና በጽድቅ በእውነትም ሁሉ ነውና ለጌታ ደስ የሚያሰኘውን እየመረመራችሁ (እያደረጋችሁ) እንደ ብርሃን ልጆች ተመላለሱ፣ ፍሬ ከሌለው ከጨለማ ሥራ ጋር አትተባበሩ>> ብሎ እንደመከረን የብርሃንን ሥራ መሥራት እንጂከጨለማ ተግባር ጋር መተባበር ለእኛ ተገቢያችን አይደለም። ኤፌ 5÷8 ጀምሮ÷

አዎ ጌታችን በገዛ ራሳችን ያመጣነውን ፍዳንና መርገምን ደምስሶ ከዲያብሎስ ክፉ አገዛዝ ነፃ ሊያወጣን ከሰማይ ወረደ÷ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ።

ሕጉንና መመሪያውን አፍርሰን፣ ትእዛዛቱንም ጥሰን በመተላለፋችን በኃጢአት ብንወድቅም እርሱ ግን በፍጥረቱ የማይጨክን ርኅሩኅ፣ ይቅር ባይ አምላክ ስለሆነ በደላችንን ሁሉ ይቅር ብሎ ከወደቅንበት ሊያነሣን መጣ።

ታዲያ አሁንስ ሕጉን መጠበቅ የለብንም እንዴ?

አዎ አሁንም ቢሆን ሕጉንና መመሪያውን እንድንጠብቅ ትእዛዛቱንም እንድንፈጽም ታዟል።

በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 14÷21 እና ምዕራፍ 15÷6 ጀምሮ ብንመለከት÷ ራሱ ጌታችን ትእዛዜን የሚፈጽም ቃሌንም የሚጠብቅ እውነተኛ ወዳጄ ነው ብሏልና እውነተኞች የእግዚአብሔር ወዳጆች ከሆን ትእዛዙን መፈጸም፣ ቃሉንም መጠበቅ ይገባናል።

ምክንያቱም እውነተኞች የእግዚአብሔር ወዳጆች መሆናችን የሚታወቀው በዚህ ነው።

አዎ ጌታችን የምትወዱኝስ ከሆነ ሕጌንና መመሪያዬን ጠብቁ ትእዛዜንም ፈጽሙ÷ ሕጌንና መመሪያዬን የሚጠብቅ፣ ትእዛዜንም የሚፈጽም ሁሉ አባቴም፣ እናቴም፣ ወንድሜም፣ እኅቴም ነው ብሎናልና፣ የእግዚአብሔርን ወዳጆች መሆን ከፈለግን፣ የእግዚአብሔር ወገኖችን ልንባል የምንወድ ከሆን ሕጉንና መመሪያውን መጠበቅ አለብን ትእዛዛቱንም መፈጸም አለብን ማለት ነው። ማቴ 12÷50 እንመልከት።

<<ያለ ሕግ ኃጢአትን ያደረጉ ሁሉ ያለ ሕግ ደግሞ ይጠፋሉና ሕግም ሳላቸው ኃጢአትን ያደረጉ ሁሉ በሕግ ይፈረድባቸዋል።

በእግዚአብሔር ፊት ሕግን የሚያደርጉ ይጸድቃሉ እንጂ ሕግን የሚሰሙ ጻድቃን አይደሉምና>> ተብሎ በጳውሎስ መልእክት ስለተነገረ። ሮሜ 2፥12

በሐዋርያው ያዕቆብ መልእክትም <<ቃሉን እየሰማ የማያደርገው የተፈጥሮ ፊቱን በመስተዋት አይቶ እንደሚሔድ ሰው ነውና ቃሉን በሰማችሁት መሠረት የምትፈጽሙት ሁኑ እንጂ እየሰማችሁ ራሳችሁን የምታስቱ አትሁኑ>> ተብሎ ስለ ተገለጸ።
ያዕ 1፥22።

ይህ ሁሉ ችግር የመጣውም አዳምና ሔዋን ሕጉን ካለማክበራቸው፣ መመሪያውንም ካለመጠበቃቸው የተነሣ መሆኑን ተገንዝበን ሕጉን የምንሰማ ብቻ ሳንሆን በሰማነው መሠረት ልንጠብቀው፣ በተማርነውም መሠረት ልንፈጽመው ይገባናል ማለት ነው ሮሜ 5፥12

አዎ የጌታችን ልደት ዋና ምክንያትንና ምሥጢሩን ከዚህ በላይ በሚገባ የተረዳን ይመስለኛል።

ስለዚህም ዘወትር በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ጉባኤ፣ በእውነተኞች መምህራን እንደሚነገረን፣ አሁንም የቅዱሳት መጻሕፍት ምሥጢራትን መሠረት አድርጎ ተደጋግሞ እንደተገለጸልን ጥልን፣ ጠብንና ጭቅጭቅን ከራሳችንም፣ከወገኖቻችንም በማስወገድ፣ ከክፋት፣ ከተንኮል፣ ከምቀኝነት፣ ከቂም፣ ከበቀል፥

በአጠቃላይ እግዚአብሔርንና ሰውን ከሚያሳዝን ተግባር ሁሉ እየታቀብን ኃጢአታችንን እየተናዘዝን ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን እየተቀበልን ለመንግሥተ ሰማያት ልንዘጋጅ፣ በተግባራዊ ፍቅር አንድ ሆነን፣ በሰላም ልንኖር፣ የልደቱ ምክንያትና መሠረታዊ ምሥጢሩ ምን እንደሆነ ተገንዝበን ትምህርቱንና ምክሩን ልብ ብለን ሰምተን በተግባር ልንተረጉመው ይገባናል።

ምንም ምክንያት ሳንሰጥም በእውነተኛው ጎዳና ዛሬ፥ ከአሁን ጀምሮ በፍጥነት ወደ ጽድቅ ሥፍራ መጓዝ አለብን።

የቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፥ የትጉሃን መላእክት፥ የቅዱሳን ነቢያት፥ የሐዋርያት፥ የጻድቃንና የሰማዕታት በረከት ረድኤት ሁል ጊዜ አይለየን።





## ክፍል <<6>>

## <<ረ>> የጌታችን ዘመነ ልደት በቅደም ተከተል ሲተነተን፥

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበት ዘመን ጠቅለል ባለ መልኩ ሲነገርና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የአቆጣጠር ሥርዓት መሠረት ሲገለጽ በ5500 ዓመተ ዓለም ፍጻሜ ነው ይባላል።

ይህ ከልደቱ በፊት የነበረው 5500 ዘመን ምሕረት፣ ሕይወት ስለአልነበረበት የመርገምና የጨለማ ዘመን በመሆኑ ዓመተ ፍዳ ዓመተ ኩነኔ በመባል ሲታወቅ፥ ከልደቱ ወዲህ ያለው ዘመን 1998 ግን ጌታችን ሰው ሆኖ፣ ከድንግል ማርያም ተወልዶ፣ ለሰው ሁሉ ፍጹም ሕይወትን፣ ፍጹም ምሕረትን፣ ድኅነትንና አንድነትን፥ ፍጹም ነጻነትንና ፍጹም ሰላምን ስለ ሰጠ ዓመተ ሥጋዌ፥ ዓመተ ምሕረት፥ ዓመተ ድኅነት እንለዋለን።
ሁለቱ 5500 እና 1998 ሲደመር ደግሞ 7498 ይሆናል።
ይህ 7498 ዘመን ዓመተ ዓለም በመባል ይታወቃል።

ይኸውም እንደ ቤተ ክርስቲያናችን አቆጣጠር ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ 7498 ዘመን ሆነ ማለት ነው።
ዓመተ ምሕረት ስንልም ጌታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ስለ አዳነን፥ ፍጹም የሆነውን ምሕረት በመስጠት ከራሱ ጋር አስታርቆ፣ ወደ ጥንታዊ መኖሪያችን ስለመለሰን፣ ኑ ወደእኔ ቅረቡ ወደ ቤታችሁም ግቡ ብሎ ወደ ራሱ፣ ወደርስቱ ስለ አቀረበን፥ የምሕረት፣ የድኅነትና የይቅርታ ዘመን ማለታችን ነው

ስለ ጌታችን ከሥጋዌው ወይም ከፅንሰቱ ጀምሮ እስከ ዕርገቱ ያለው ዘመን እያንዳንዱ ሲተነተንም፥5500 ዓመተ ዓለም፣ ዘመነ ዮሐንስ መጋቢት 29 ቀን ትስብእቱ፥ (ፅንሰቱ)

5501 >> >> >>>> ወይም በ1ኛው ዓ ም መጨረሻ በ2ኛው ዓ ም መጀመሪያ ዘመነ ማቴዎስ ታኅሣሥ 29 ቀን ልደቱ፥5530 >> >> >>>> ወይም በ30 ዓ ም ዘመነ ሉቃስ ጥር 11 ቀን ጥምቀቱ (በ30 ክረምቱ ተጠመቀ ይላል ማቴ 3፥13 ትርጓሜው) 5533>> >>>>>> ወይም 33 ዓ ም ከ3ወር ዘመነ ማርቆስ መጋቢት 27 ቀን ስቅለቱ፥ በ3ኛ ቀኑም በዚሁ ዘመን መጋቢት

# ምዕራፍ 3

# <<ጥምቀት>>

## በዚህ ጥምቀት በሚል ርእስ መነሻ፥ ከዚህ ቀጥለው ያሉትን፥ ማለትም፤

<<ሀ>> ስለ ጥምቀት ቀጥተኛ ትርጉምና መሠረታዊ ምሥጢሩ፥

<<ለ>> ስለ ጥምቀት አስቀድሞ የተነገረው ትንቢትና ፍጻሜው፥

<<ሐ>> ስለ ጥምቀትና መሠረታዊ ጥቅሙ በሐዲስ ኪዳን፥

<<መ>> ወንድ ልጅ በተወለደ በ40 ቀኑ፥ ሴት ልጅ በተወለደች በ80 ቀኗ እንዲጠመቁ የመደንገጉ ምክንያትና ዋና መሠረታዊ ምሥጢሩ፥

<<ሠ>> ስለ ግዝረት መሠረታዊ አመጣጥና ጥቅሙ፤ በሐዲስ ኪዳን ያለውም፥

<<ረ>> ስለ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት፥

<<ሰ>> ታቦታት በልዩ ልዩ ዝማሬ እየታጀቡ ወደ ባሕረ ጥምቀት መውረዳቸው፥

<<ሸ>> ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ሔዶ በፈጠረው፤ በባሪያው (በአገልጋዩ) በዮሐንስ እጅ የመጠመቁ ምሥጢር፥

እነዚህንና ከእነዚህ ጋር የተያያዙትንም ምሥጢራት ዐጠር ባለ መልኩ ደረጃ በደረጃ እንመለከታለን።





# ክፍል 7

## <<ሀ>> የጥምቀት ቀጥተኛ ትርጉምና መሠረታዊ ምሥጢሩ፥

ጥምቀት **<<**አጥመቀ አጠመቀ**>>** ከሚል የግእዝ ግስ የሚገኝ ዘር ነው።

ጥምቀት በነጠላ ትርጉም ሲተረጉም (ቀጥተኛ ትርጉሙ) ሰውነትን በውሃ መጠመቅ፥ ውሃ ውስጥ መጥለቅ፤ ውሃ ውስጥ ገብቶ መታጠብ፥ በውሃ መረጨት ማለት ሲሆን፥

ምሥጢራዊ ትርጉሙም፥ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም በውሃ ተጠምቆ ስመ ክርስትናን መቀበል፥

ክርስቲያናዊ የክርስቶስ ወገን መባል፤ የመንፈስ ቅዱስ ልጅ መሆን ማለት ነው።

# ክፍል <<8>>

## <<ለ>> ስለ ጥምቀት በብሉይ ኪዳን አስቀድመው ከተነገሩት ትንቢታት መካከል፥

<<1>> በትንቢተ ኢሳይያስ እንደምንመለከተው እግዚአብሔር ያዕቆብን፥ **<<**በተጠማ ላይ ውሃን፥ በደረቅም መሬት ላይ ፈሳሾችን አፈስሳለሁና መንፈሴን በዘርህ ላይ በረከቴንም በልጆችህ ላይ አፈስሳለሁ**>>** ብሉታል። ኢሳ 44፥3።

<<2>> በትንቢተ ሕዝቅኤልም፥**<<**ጥሩ ውሃንም እረጭባችኋለሁ፥ እናንተም ትጠራላችሁ ከርኩሰታችሁም ሁሉ፤ ከጣዖታችሁም ሁሉ አጠራችኋለሁ።

አዲስም ልብ እሰጣችኋለሁ አዲስም መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ**>>** ብሏል።

በጥምቀት የአዲስ ልደት እንደምንወለድ አስቀድሞ ትንቢቱ ተነግሯል ማለት ነው። ሕዝ 36፥25።

<<3>> ነቢዩ ሚክያስም ስለ መድኃኒታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአትን የማስተስረይ አምላካዊ ሥራ ሲገልፅ፥

<<ተመልሶ ይምረናል ክፋታችንን ይጠቀጥቃል ኃጢአታችንንም በባሕሩ ጥልቅ ይጥለዋል>> በማለት አስቀድሞ ተናግሯል። ሚክ 7፥19

ይኸውም ዲያብሎስ አዳምንና ሔዋንን የእርሱ ተገዥዎች፣ አገልጋዮቹ እንደሆኑ አስመስሎ፣ አታሎ በማጻፍ በሲኦልና በባሕር አስቀምጦት የነበረውን የዕዳና የጥፋት ውል ደምስሶ ከኃጢአት ነፃ እንደሚያደርገን ጌታችን ስለገለፀለት ነው ትንቢቱን አስቀድሞ የተናገረ።

<<4>> መጥምቁ ዮሐንስ ደግሞ ቀደም ብሎ በነቢዩ ኢሳይያስ በተነገረው መሠረት፥ <<እኔ ለንስሓ በውሃ አጠምቃችኋለሁ እርሱ ግን በመንፈስ ቅዱስ በእሳትም ያጠምቃችኋል>> ብሎ ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጥምቀት አማካይነት ልጅነትን የመስጠት አምላካዊ ሥራ ገልጾአል። ማቴ 3፥11 ማር 1፥1 እና ዮሐ 1፥26 እንመልከት።

መጥምቀ መለኮቱ ቅዱስ ዮሐንስ አስቀድሞ እንደገለፀልን የዮሐንስ ጥምቀት በውሃ ሆኖ ለንስሓ ለዝግጅት ነበር እንጂ ልጅነትን አላሰጠም።

የጌታችን ጥምቀት ግን በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ስለ ሆነ የመንፈስ ቅዱስ ልጅነትን ያሰጣል።

አዎ ከጌታችን የምናገኘው ጥምቀት ፍጹም ልጅነትን የሚያሰጥ ለስርየተ ኃጢአት፣ ለፍጹም ነፃነት፣ ለዲያብሎስ ድል መንሻ፣ ለመንግሥተ ሰማያት መውረሻ የሚያበቃ ነው። ከዚህ በስተቀር ለመንግሥተ ሰማያት መብቃት አይቻልም።

ምክንያቱም በቅዱስ ወንጌሉ ጌታችን አምኖ የተጠመቀ ይድናል፥ አምኖ ያልተጠመቀ ግን አይድንም ብሎ ስለተናገረ በእግዚአብሔር የባሕርይ አምላክነት፣ በእዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት፣ በእግዚአብሔር ፍጹም አዳኝነት አምኖ ያልተጠመቀ ፍጹም ድኅነት፣ ፍጹም ሕይወት የለውም። ማር 16፥16

አዎ ሰው ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ ከማኅፀነ ዮርዳኖስ





ካልተወለደ፥ ማለትም ይህችን ልጅነትን የምታሰጠው ጥምቀት በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም በውሃ ያልተጠመቀ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ልጅ እንደማይባልና ወደ መንግሥተ እግዚአብሔርም (ወደ መንግሥተ ሰማያትም) ፈጽሞ መግባት እንደማይችል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ወንጌልም ነግሮናል። ዮሐ 3፥5።

አስቀድሞ በልዩ ልዩ ቅዱሳት መጻሕፍት ተጽፎ፣ በነቢያት ልሳን (አንደበት) በትንቢት መልክ ተነግሮ በየክፍሉ ተዘግቦ የምናገኘው ቅዱስ ቃልም ለጊዜው በወቅቱ ለነበሩት ይሁን እንጂ የትንቢቱ ፍጻሜ ግን ጌታችን በዘመነ ሥጋዌው ስለሚሠራው አምላካዊ ሥራ፣ ስለ መድኃኒታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ምሥጢር የሚመለከት እንደመሆኑ መጠን በሐዲስ ኪዳን በእየደረጃው ተፈጽሞ እናገኘዋለን።

## ክፍል <<9>>

## <<ሐ>> ስለ ጥምቀትና መሠረታዊ ጥቅሙ በሐዲስ ኪዳን፥

ስለ ጥምቀት በሐዲስ ኪዳን ከተጠቀሱት መካከል ከዚህ ከፍ ብሎ በመ ተራ ፊደል የተገለጸው እንዳለ ሆኖ ጥቂቶችን ደግሞ ለምሳሌ ያህል ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን።

ጌታችን ደቀ መዛሙርቱ ሐዋርያትን <<እንግዲህ ሒዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው>> ብሏቸዋል።

ማቴ 28፥18

ይህ ትእዛዝ ለጊዜው ለሐዋርያት ቢሆንም፥ በሐዋርያት እግር ተተክተው የሐዋርያትን ሥራ የሚሠሩ እስከ ምጽአቱ ድረስ የሚነሡትንም ካህናትን ሁሉ ይመለከታል።

ቃሉ ሲብራራም ያልተማሩትን እያስተማራችሁ፣ ያላመኑትንም እያሳመናችሁ፣ ያልተጠመቁትን ሁሉ እያጠመቃችሁ የክርስቶስ ተከታዮች የክርስቶስ ወገኖች ክርስቲያኖችን አድርጓቸው ማለት ነው።

አዎ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ አምኖ የተጠመቀ ሁሉ

የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ልጅ ስለ ሆነ በእግዚአብሔር ማኅበር ገብቶ በክርስቶስ አንድነት ይኖራል።

በመሆኑም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፥ <u>በገላትያ ምዕ 3፥26 መልእክቱ፥</u> <<በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ስለ ሆናችሁ ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ክርስቶስን ለብሳችኋልና በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁ>> ብሎአል።

<u>በቲቶ 3፥4 መልእክቱ እንደምንረዳውም፥</u> በካህኑ አማካይነት በመንፈስ ቅዱስ ስም በውሃ <u>ወንድ ልጅ በተወለደ በ40 ቀኑ፤ ሴት ልጅ በተወለደች በ80 ቀና አንድ ጊዜ ብቻ</u> የምንጠመቀው ጥምቀት ከማኅፀነ ዮርዳኖስ ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ በአዲስ ልደት ተወልደን የእግዚአብሔር ልጆች የምንባልበት፤ ስመ ክርስትናን የምናገኝበት፤ የክርስቶስ ወገኖች፤ ክርስቶሳውያን ክርስቲያኖች መሆናችንን የምንታወቅበት ልዩ ስጦታችን ነው።

<u>ጥምቀት</u> ለንስሓ፤ ለስርየተ ኃጢአት የተሰጠ ሁብተ መንፈስ ቅዱስ ነው።

<u>ስለዚህም</u> ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፋዊ ሥርዓቱንና ሃይማኖታዊ ትውፊቱን ከሊቃውንት አባቶቻችን ተቀብላ ስትፈጽመው ስታስፈጽመው ትገኛለች።

በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖታዊ ትውፊት (<u>ቅብብሎሽ</u> መሠረት በየዓመቱ የምናከናውነው የጥምቀት ሥርዓት የጌታችንን ጥምቀት ለማስታወስ፤ በዐሉን ለማክበር፤ ትምህርቱን በተግባር ለማስተማር፤ መንፈሳዊ ሥርዓቱና ባህሉ ለሁሉም ሕዝበ ክርስቲያ ግልፅ ሆኖ እንዲሰራጭ፤ ጥንታዊ የሆነ መንፈሳዊ ታሪኩም ለመላው ዓለም በተግባራዊ ትምህርት መልክ እንዲዳረስ ለማድረግ ሲሆን፤

እንዲሁም በውስጡ እያዳንዳችን ከበቀል፤ ከቂም፤ ከሐሜት፤ ከቅንዓት፤ ከምቀኝነት፤ ከጥላቻ፤ ከተንኮልና ከመሳሰለው የኃጢአት ተግባር ሁሉ ንጹሓን መሆን ተገቢያችን እንደሆነ የሚነግረን፥ እግዚአብሔርንና ሰውን ከሚያሳዝን ሥራ እንድንርቅም የሚመክረን፤ ኃጢአታችንን እየተናዘዝን ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን እየተቀበልን ለመንግሥተ ሰማያት መዘጋጀት እንደሚገባን የሚያስገነዝበን ዐቢይ መልእክት ያለበት ነው።

ስለዚህም እያንዳንዳችን ትምህርቱንና ምክሩን ከልብ ተቀብለን በተግባር ልንተረጉመው ይገባናል ማለት ነው።





## <u>ክፍል <<10>></u>

### <u><<መ>> ወንድ ልጅ በተወለደ በ40 ቀኑ፥ ሴት ልጅ በተወለደች በ80 ቀኗ እንዲጠመቁ የመደንገጉ ምክንያት፥</u>

ወንድ ልጅ በተወለደ በዐርብዓ ቀኑ፥ ሴት ልጅ ከሆነች ግን በተወለደች በሰማኒያ ቀኗ እንዲጠመቁ መወሰኑ ደግሞ መዋዕለ ንጽሕ፤ ወይም የንጽሕና ጊዜ፥ ወንድ ልጅ በተወለደ በ40 ቀኑ፥ ሴት ልጅ በተወለደች በ80 ቀኗ ስለሚፈጸም ሲሆን፥

ምሳሌውም አዳም በተፈጠረ በ40 ቀኑ፥ ሔዋንም በተፈጠረች በ80 ቀኗ በመላእክት ታጅበው ገነት ስለ ገቡ እንደሆነ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ይናገራሉ፤ ቅዱሳት መጻሕፍትም ያመሠጥራሉ። <u>ዘፍ 2፥8</u>

<u>በኦሪት ዘሌዋውያን</u> ተዘግቦ እንደምናገኘው በሙሴ ዘመንም ወንድ በተወለደ በ40 ቀኑ፤ ሴት በተወለደች በ80 ቀኗ ወደ ቤተ መቅደስ እየሔዱ የእግዚአብሔርን በረከት እንዲቀበሉ በእግዚአብሔር ታዟል። <u>ዘሌ 12፥1</u>

## <u>ክፍል <<11>></u>

### <u><<ሠ>> ስለ ግዝረት መሠረታዊ አመጣጥና ጥቅሙ፥</u>

የስምንት ቀን ወንድ ልጅ ሁሉ እንዲገረዝ በእግዚአብሔር ታዟል <u>ዘፍ 17፥10 በዘፍጥረት ምዕ 17፥9 ጀምሮ</u> እንደምንመለከተው በኦሪት ሥርዓት በጥምቀት ፈንታ ግዝረት የአሕዛብ፥

ማለትም የአረማውያንና የእግዚአብሔር አማኞች መለያ፤ የእምነት ምልክት፤ የቃል ኪዳን መሠረት እንደ ነበር ይታወቃል።

በኦሪት ዘመን በ8ኛው ቀኑ ያልተገረዘ ሁሉ ከአብርሃም ቤተ ሰብ እንዲቆጠር፤ ምድረ ርስት እንዲወርስ፤ ከተስፋውም እንዲካፈልና የእግዚአብሔር ወገንም እንዲባል ሥርዓቱ ፈጽሞ አይፈቅድለትም ነበር።

(በ30 ዓመቱ) ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ሔዶ የእርሱ ፍጡር በሆነው በባሪያው በዮሐንስ እጅ ሊጠመቅ ችሏል።

ዮሐንስ ሌላውን ሳጠምቅ በአንተ ስም አጠምቃለሁ አንተንስ በማጠምቅበት ጊዜ አቤቱ ምን እላለሁ? (በማን ስም ላጥምቅህ) ብሎ ጌታን ቢጠይቀውም **«ነዋ በግዑ ለእግዚአብሔር ዘያእትት ወያሴስል ኃጢአተ ዓለም (ኃጢአተ እምዓለም) ወልዱ ለቡሩክ ከሣቴ ብርሃን በል»** ዮሐ.1፥29።

አለውና እነሆ የሰውን ኃጢአት የሚያስተሰርይ (የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ) የእግዚአብሔር በግ, መሥዋዕት (የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅ) በማለት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አጠመቀው።

በጥምቀቱ ጊዜም እግዚአብሔር አብ አንድ አካል አንድ ባሕርይ አድርጎ ለተዋሕዶ የመረጥኩት በእርሱ ህልው ሆኜ ልመለክበት የወደድኩት የባሕርይ ልጄ ይህ ነውና እርሱን ስሙት በማለት በደመና ላይ ሆኖ ሲመሰክርለት ተሰምቷል፣ መንፈስ ቅዱስም በርግብ አምሳል ወርዶ በራሱ ላይ ሲቀመጥ ታይቷል።

ማር 1፥9, ሉቃ 3፥21, 9፥35, 2ኛ ጴጥ 1፥16።
<<በአበው ትርጓሜ መሠረት ሲብራራ ነው>>

ይኸውም ከቅዱሳት መጻሕፍት ታሪክ እንደምንረዳው፥ ርግብ ቂምንና በቀልን ስለማትይዝ መንፈስ ቅዱስም ጎዳጌ አበሳ ጎዳጌ በቀል፥ (ይቅር ባይ) እንደሆነ ይታወቃልና መንፈስ ቅዱስን በርግብ ይመስለዋል።

ርግብ በኖኅ በማየ አይኅ ጊዜ፥ ማለትም በኖኅ የጥፋት ውሃ ጊዜ ሐጸ ማየ አይኅ ነትገ ማየ አይኅ፥ የጥፋት ውሃ ጉደለ ስትል የዕፀ ዘይትን ቅጠል በአፏ ይዛ በብሥራት ምልክት የምሥራች እያለች የተገኘች ስትሆን መንፈስ ቅዱስም ተስፋ መስቀልን፥ ማለትም ጌታችን በመስቀል ተሰቅሎ የሚሰጠውን ድኅነት ያበሥራል።

ርግብ ክንፏን ቢመቷት ዕንቍላሏንም ቢሰብሩባት ቤቷን ካላፈረሱባት መኖሪያዋን ለቃ እንደማትሔድ ሲታወቅ መንፈስ ቅዱስም ፈጽመን ካልካድነው በስተቀር ኃጢአትን ብንሠራም እንኳ ጨርሶ አይለይንም ንስሓ እንድንገባ ጊዜ ይሰጠናል በአጠገባችን ሆኖ ይጠብቀናል፥ ብንበድልም በንስሓ ከተመለስን ይቀርባል፣ መጥቶም በእኛ ላይ ያድራል ማለት ነው።





ለዚህ በትርጓሜ ወንጌል ማቴ 3፥17 የሚገኝ ታሪካዊ ምሳሌ አለው፥

ይኸውም አንድ መነኩሴ የገልፎ ልጅ ቆንጆታ (ተውባ) ስለአያት ልቡ በሐጸ ዝሙት ተነድፎ ፈተና ላይ ወደቀና ልጂቱን ሳገባሽ አላት።

እርሷም አባቴ ሳይፈቅድ አይሆንም ነገር ግን ብትጠይቀው እንቢ አይልህምና አባቴን ጠይቀው እርሱ ከፈቀደ ይሆናል አለችው።

መነኩሴውም ገልፎ የሚባለውን አባቷን ስጠኝ ፍቀድልኝ ብሎ ጠየቀው እርሱም አምላኬን ልጠይቅ ብሎ የሚያመልከውን ጣዖቱን ቢጠይቅ መጀመሪያ ፈጣሪውን ይካድ ቆቡንም ይቅደድ አለው።

ገልፎም ተመልሶ መጥቶ መነኩሴውን ፈጣሪህን ካድ ቆብህን ቅደድና ልፍቀድልህ አለው።

መነኩሴው ልጂቱን ለማግኘት ቸኩሎ ነበርና ያለውን ሁሉ አደረገ ፈጣሪውን ክዶ ቆቡንም ቀድዶ ያልከኝን ሁሉ አድርጌአለሁና ስጠኝ አለው።

አሁንም ሒጄ ልጠይቅ ብሎ ሔዶ ጣዖቱን ቢጠይቅ መንፈስ ቅዱስ ፈጽሞ አልተለየውም በአጠገቡ ሆኖ ይጠብቀዋልና ፈጽሞ እስኪለየው ድረስ እትስጠው አለው።

መነኩሴው እሺ አሁንስ ቢለው ገልፎም ተነግሮታልና አይሆንም ቆይ ጠብቅ አለው።

በዚህ ጊዜ መነኩሴው የፈለኩትን ሳላገኝ፥ ያውም ለኃላፊ ለጠፊ ምኞት ስል ፈጣሪዬን ካድኩ፣ ቆቤንም ቀደድኩ ብሎ ከልቡ አዝኖ አልቅሶ ንስሓ ቢገባ ፈጽሞ አልተለየውም ነበርና መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል መጥቶ ሲያድርበት ታይቷል።

ይኸውም በተግባሩ ተፀፅቶ በንስሓ ወደ እግዚአብሔር በመመለሱ ነው።

ይህ ሁሉ ሲሆን ለመነኩሴው አልተገለጸለትም፥ ነገር ግን ለአንድ የበቃ ንጹሕ ባሕታዊ ምሥጢሩ ተገልጾለት ይመለከት እንደ ነበር በታሪኩ ተጠቅሷል።
<<ከአበው ትርጓሜ ማቴ 3፥1 የተጠቀሰ ነው>>

እኛም ተሳስተን ብናጠፋ፣ ኃጢአትን ብንሠራም እንኳ ተስፋ በመቍረጥ እኔ ኃጢአተኛ ስለ ሆንኩ እግዚአብሔር አይምረኝም ማለት የለብንም። እንደዚህ የምንል ከሆን በእግዚአብሔር ፍጹም አምላክነትና ፍጹም መሓሪነት አንተማመንም ማለት ነው።

<u>ምክንያቱም</u> እግዚአብሔር የምሕረትና የይቅርታ አምላክ እንጂ ጨካኝ አይደለምና ከሁሉ በፊት ኃጢአትን ከመሥራት፣ ከመበደል መቆጠብ፣ መጠንቀቅ ተገቢ ሲሆን፥ መቸም ሰው በተፈጥረውም ደካማ ነውና ተሳስተን ከበደልን ደግሞ ምሕረትን በሚያስገኝ መልካም ሥራ፣ በዓውደ ምሕረት (በቅዱስ መካን) በእግዚአብሔር ቤት ተገኝተን፥ በበደላችን ተፀፅተን፣ ከልባችን አልቅሰን፣ ንስሓ ገብተን አምላካችንን ብንለምን እግዚአብሔር ፈጣሪአችን የርኅራኄና የጽድቅ ባለቤት፣ ይቅር ባይ፣ መሐሪ አምላክ ስለሆነ ይምረናል፣ በደላችንን ይቅር ይለናል መንፈስ ቅዱስም አይለየንም ማለት ነው።

<u>ስለዚህ</u> በፍጥረቱ የማይጨክን ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ፍጹም አምላክ ሲሆን ሊያድነን ስለ ፈቀደ ወደዚህ ዓለም መጥቶ፣ ፍጹም ሰው ሆኖ፣ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ፣ በዮርዳኖስ ባሕርና በሲኦል የነበረውን የጥፋት ውላችንን ሁሉ ደምስሶ፥ ፍጹም የሆነውን ዘለዓለማዊውን ሕይወት ሰጥቶናልና እኛም በተከታዮቹ በመምህራን አማካይነት በየጊዜው፥ በየክፍሉ የሚቀርብልንን ንጹሕ የሆነውን የእርሱን ቃል እየሰማን በተግባር ላይ ማዋል ይገባናል።

አዎ ሁል ጊዜ በሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን፥ በአባቶቻችንና በካህናት የሚሰጠንን ጠቃሚ ምክር እየተቀበልን ሕጉንና መመሪያውን መጠበቅ፥ ትእዛዛቱንም መፈጸም አለብን። የሃይማኖት መታወቂያው መልካም ምግባር ነውና ሃይማኖታውያን መሆናችንን በመልካም ሥራ መግለጽ ያስፈልገናል ማለት ነው። ሃይማኖታችንን ከመልካም ምግባር ጋር ይዘን፥ በማየ ንስሓ (በንስሓ ውሃ) ታጥበን፣ ከኃጢአት ሁሉ ንጹሓን በመሆን ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን እየተቀበልን ወደ ገነት፣ ወደ መንግሥተ ሰማያት እንድንገባ የእርሱ መልካም ፈቃድ ይሁንልን።

የቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፥ የትጉሃን መላእክት፣ የቅዱሳን፣ የነቢያት፣ የሐዋርያት፣ የጻድቃንና የሰማዕታት በረከት ረድኤት ሁል ጊዜ አይለየን።

ስብሐት ለእግዚአብሔር ለዘአብጽሐነ እስከ ዛቲ ሰዓት፤ ከዚህ ዕለት ከዚህ ሰዓት ላደረሰን ለእግዚአብሔር አምላካችን ምስጋና ይድረሰው።





# <u><<ቃና ዘገሊላ፥>></u>

# <u>ምዕራፍ <<5>></u>

## <u>ቃና ዘገሊላ፥</u>

በዚህ ቃና ዘገሊላ በሚለው ርእስ ስለ ቃና ዘገሊላና የቃና ዘገሊላ መሠረታዊ ምሥጢርን እንመለከታለን።

## <u>ክፍል <<15>></u>

<u>የዕለቱ ምስባክ በልሳነ ግእዝ (በግእዝ ቋንቋ) ሲነገር፥</u>

<<እስመ መምህረ ሕግ ይሁብ በረከተ
ወየሐውር እምኃይል ውስተ ኃይል
ወያስተርኢ አምላከ አማልክት በጽዮን>>
ይላል።

<u>በአማርኛ ሲተረጐምም፥</u> የሕግ መምህር በረከትን ይሰጣልና ከኃይል ወደ ኃይል ይሔዳል፥ የአማልክት አምላክ በጽዮን ይታያል ማለት ነው። <u>መዝ 83፥6።</u>

<u>ይህ መዝሙር ከመጀመሪያው</u> ልበ አምላክ የተባለው ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት አቤቱ የኃያላኑ ባለቤት በማለት ፈጣሪው እግዚአብሔርን ያመሰገነበት ሲሆን፥ አለፍ ብሉ ከቍጥር 6 ደግሞ ሕግን የሠራ የወሰነ ያስተማረ መምህረ ሕግ ኢየሱስ ክርስቶስ በረከተ ሥጋን በረከተ ነፍስን ይሰጣልና ከኃይል ወደ ኃይል፥ ማለትም ድልን ከማድረግ ወደ ድል ማድረግ፣ ተአምራትን ከማድረግ ተአምራትን ወደ ማድረግ ይሔዳል፤

ጣዖታትን ቀጥቅጦ አጥፍቶ የእርሱ አገልጋዮች የሚሆኑ ካህናትን ያዘጋጀ (የመደበ) ልዑል እግዚአብሔር በኢየሩሳሌም በረድኤት ተገለጠ።

ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ በማለት የእግዚአብሔርን አምላካዊ ሥራ የሚገልጽ ምሥጢርን ያመሠጠረበት ነው።

<u>በመዝሙር 45፥7ም</u> ከዚህ ጋር በተመሳሳይ የኃያላኑ ባለቤት አምባ መጠጊያችን የሚሆን የያዕቆብ ፈጣሪ በረድኤት፣ (በባሕርይ አምላክነት) ከእኛ ጋር አለ። መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል እመቤታችንን ትፀንሽያለሽ ወንድ ልጅንም ትወልጅያለሽ ብሉ ደስ ካሰኛት ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደ አምላካችን በረድኤት ከእኛ ጋር ነው የሚል ምሥጢር ይገኛል።

<u>ነቢይ ዳዊት በመዝሙር 86፥3 ደግሞ፥</u> <<ነኪር ነገሩ በእንቲአኪ ሀገረ እግዚአብሔር>> እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን የእግዚአብሔር ከተማ (ማደሪያ) ሆይ ስለ አንቺ (በአንቺ) የተደረገው ሁሉ ዕፁብ ድንቅ ነው በማለት አስቀድሞ በትንቢታዊ ምሥጢር አመስግኗታል ዘምሮላታልም።

ይኸውም አምላክን ያለ ዘርና ያለ ሩካቤ በድንግልና ፀንሳ፣ በድንግልና መውለድዋ ፈጽሞ የማይመረመር አምላካዊ ጥበብ፣ አምላካዊ ሥራ ነውና ስለ አንቺ የተነገረ፣ ባንቺ ምክንያት የተገኘ ሕይወት፣ የተፈጸመው ተስፋና ለአንቺ የተደረገ ሁሉ በፍጡር ሊለካ የማይቻል ዕፁብ ድንቅ የሆነ አምላካዊ ሥራ ያለበት ምሥጢር ነው ማለት ነው።

<u><<በአበው ትርጓሜ መሠረት ሲብራራ ነው>></u>

አዎ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማኅፀኗን ዓለም አድርጎ 9 ወር ከ5 ቀን ሲመሰገንባት ኑሯልና እመቤታችን ሀገረ እግዚአብሔር (የእግዚአብሔር ሀገር, የእግዚአብሔር ከተማ, የእግዚአብሔር ማደሪያ) ትባላለች።

<u>(በትርጓሜው ሲብራራ)</u> እግዚአብሔር እመቤታችንን በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ አፀናት።

ከቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜና ከሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አባቶቻችን እንደምንረዳው 3 አካላት አድረውባታል ይላል።

(አብ, ወልድ, መንፈስ ቅዱስ ማለታችን ነው)።

<u>ይኸውም</u> አብ ለአጽንኦ፥ መንፈስ ቅዱስ ለአንጽሖ፥ ወልድ በተለየ አካሉ ለመዋሐድ፣ ለመከፈል (ለመወለድ ነው)። ለአንጽሖ ሲልም ነውርና ኃጢአት ኑሮባት ሳይሆን ጠበቃት (ከለከላት) ማለት ነው ብሉ <u>በማቴዎስ ወንጌል 1፥18 በትርጓሜው</u> አመሥጥሮታል።





ምክንያቱም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከኃጢአትና ከነውር ሁሉ ንጽሕት የሆነች፣ በዘመናችን አንድ አንድ ሰዎች ጥንተ አብሶ እያሉ የሚጠሩትም ፈጽሞ የሌለባት ናት።

አዎ እግዚአብሔር አብ በነቢያት አድሮ በእርሱ ህልው ሁኜ የምመሰገንበት የምወደው ልጄ ይወርዳል ይወለዳል ብሉ ትንቢትን ተናገረ፣ አካላዊ ቃሉን ለኩነተ ሥጋ ሰጠ።

<u>ማለትም <<ቃለ አብ ሕያው ዘወረደ እምሰማያት,(ቃሉ ለአብ>></u> የአብ ቃል የሚባል የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅ እግዚአብሔር ወልድ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን፣ ከነፍሷም ነፍስን ነሥቶ ተዋሐደ።

ይኸውም ትስብእት ከእመቤታችን ተከፈለ የያዕቆብ ፈጣሪ፣ የኃያላኑ ባለቤት እግዚአብሔር ፍጹም የባሕርይ አምላክ ሲሆን፥ ከእኛ ጋር ተዋሐደ፥ ከሥጋችን ሥጋን ከነፍሳችንም ነፍስን ነሥቶ (ተዋሕዶ) ፍጹም ሰው ሆነ፣ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ ማለት ነው።

በመሆኑም ከላይ <u>በተገለጸው መዝሙር</u> 45 በዚህ ዓለም ወይም በቃና ዘገሊላ ያደረገውን የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ፣ ተአምራቱን ሁሉ ታዩ ዘንድ በዕግረ ኀሊና ኑ ይለናል።

ስለዚህም ከአምልኮ ባዕድ ወደ አምልኮ እግዚአብሔር፥ ከትዕቢት ወደ ትሕትና፥ ከክፋትና ከተንኮል፣ ከምቀኝነትም ወደ የዋህነት፥ ከቂምና ከበቀልም ወደ ይቅር ባይነት ተመልሰን በንጹሕ ልብ ወደ እግዚአብሔር አምላካችን ልንቀርብ ይገባናል።

## <u>ክፍል <<16>></u>

### <u>ስመሆኑ ቃና ዘገሊላና የቃና ዘገሊላ መሠረታዊ ምሥጢር ምንድ ነው?</u>

ቃና ኢየሩሳሌም አካባቢ በገሊላ አውራጃ (አጠገብ) የምትገኝ መንደር እንደሆነች ይታወቃል።

<u><<ወእመ ሣልስት ዕለት ከብካብ ኮነ በቃና ዘገሊላ ዮሐ 2፥1</u>

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማሪያም ከተወለደ በኋላ በትንሽ በትንሽ አድጎ፣ በ30

(የወይኑ አሳላፊዎችን) ማለትም ወይኑን የሚያቀርቡትን ጌታ የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ አለቻቸው። ጌታችንም አገልጋዮችን ጋኖችን ውሃ ቀድተው እስከ አፋቸው ድረስ እንዲመሉዋቸው አዘዛቸው።

እነዚያ የድንጋይ ጋኖች 6 ሲሆኑ እያንዳንዳቸው ሁለት፣ ሁለት፥ ወይም ሦስት፣ ሦስት እንስራ የሚይዙ እንደ ነበሩ ቅዱስ መጽሐፉ ይገልጻል።

አገልጋዮችም ጌታ እንዳዘዛቸው ጋኖቹን እስከ አፋቸው ድረስ ውሃ መሉዋቸው።
ጌታችን አሁን ቀድታችሁ ለአሳዳሪው (ለሊቀ ምርፋቅ) ስጡት አላቸውና ቀድተው ለሊቀ ምርፋቅ ቢሰጡት ውሃው ወደ ወይን ተለውጦ ልዩና መልካም የሆነ ጣዕምን ስለ አመጣ ሊቀ ምርፋቅ የወይን ጠጅ የሆነውን ውሃ በቀመሰ ጊዜ እጅግ ተደነቀ። እንደዚህ የሆነበትን ምሥጢር ግን አላወቀም ነበርና ሙሽራውን ዶኪማስ ብሎ ጠርቶ ሰው ጥሩውን በመጀመሪያ ያቀርባል እንጂ እንዴት ሰው ጥሩውን አቆይቶ አሁን ሰው ከጠገበ በኋላ ይሰጣል አለው ይላል ቅዱስ ታሪኩ።

አዎ ይህ ድንቅ የሆነ አምላካዊ ሥራ የጌታችን የመጀመሪያ ተአምራት ነው ተብሎ ይነገራል።

ከዚህ ቀጥሎም ደቀ መዛሙርቱን እያስከተለ፣ እያስተማረ፣ ጥቂቱን ኢያበረከተ እየመገበ፣ ድውያንን እየፈወሰ፥ በአጠቃላይ ልዩ ልዩ ተአምራትንና አምላካዊ ሥራዎቹንም እየሠራ ቆይቶ ጊዜው ሲደርስ በመስቀል ተሰቅሎ ፍጥረቱንና ዓለምን ሁሉ አዳነ።

አልደረሰም የተባለው ጊዜም ስለ ደረሰ እንኩ ብሉ፣ ጠጡም ብሎ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ሰጠን። መምህረ ሕግ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በረከተ ሥጋንና በረከተ ነፍስን ያሳድርብን።

የቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፣ የቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት፣ የሁሉም ትጉሃን መላእክት፣ የቅዱሳን ነቢያት፣ የሐዋርያት፣ የጻድቃንና የሰማዕታት በረከት፣ ረድኤት ሁል ጊዜ አይለየን።

ከዚህ ዕለት ከዚህ ሰዓት ስለ አደረሰንም ምስጋና
ለእርሱ ይሁን
አሜን።





## ምዕራፍ <<6>>

## <<ጾምና ጸሎት>>

በዚህ ጾምና ጸሎት በሚል ርእስ መነሻ፥

<<ሀ>> ጾም ማለት ምን ማለት ነው?

<<ለ>> አፈጻጸሙስ እንዴት ነው?

<<ሐ>> ጸሎትስ?

<<መ>> ጾምና ጸሎት ለምን ይጠቅማል? ከምንስ ያድናል?

<<ሠ>> ጾም በብሉይ ኪዳን፥

<<ረ>> ጾም በሐዲስ ኪዳን፥

<<ሰ>> በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖታዊ ቀኖና ፍትሐ መንፈሳዊ አንቀጽ 15 እንዲጾሙ የተመደቡት አጽዋማት ቍጥርና የስማቸው ዝርዝር፣

<<ሸ>> ዐቢይ ጾም ማለት ምን ማለት ነው?

<<ቀ>> ዘወረደ ማለት ምን ማለት ነው?

<<በ>> የዘወረደ ጾምስ ምንድ ነው?

<<ተ>> ዐቢይ ጾም፥ ጾም እስከ ስንት ሰዓት ነው የሚጾመው?

<<ቸ>> ንስሐ ምንድ ነው?

<<ኀ>> ሰንበትና የሰንበት መሠረታዊ ምሥጢር ምንድ ነው? የሚሉትን በየክፍላቸው እንመለከታለን።

ምክንያቱም እንደበቱ ተቆላልፏል፣ እጁና እግሩም ተሰነካክለዋል፣ (ተሳሥረዋል) የሚያነጋግረው ባዕድ (ሌላ) ነው፣ መሪውን የያዘውም ሌላ ነው።

አዎ ነጂው ሌላ ስለ ሆነ ነጂው ወደ ወሰደው ዝም ብሉ ይነዳል ማለት ነው።

ታዲያ በዚህ ሁኔታ ውስጥ የገባ ሰው አለሊባል ይቻላል?

በዚህ ሁኔታ ውስጥ የገባ ሰውኮ የሚናገረውንምሆነ የሚያደርገውን ነገር ሁሉ አያውቅምና በቁሙ ሙቷል ማለት ነው፥ ወደ ኃጢአት ሞትም እየተጓዘ ነው።

ስለዚህ ይቅር በጾም ወቅት በሌላውም ጊዜ ቢሆን ከዚህ መጠንቀቅ አይገባምን?

አዎ መጾም ማለትም ሥጋችንን ከሥጋዊ ፍላጎት መከልከል፣ <u>በማቴ 5፥6 ጀምሮ</u> በሰፊው እንደተገለጸው የሚያምረውንና የሚያስጉመዥውን ጊዜያዊ ደስታን ስለ ዘለዓለማዊ ደስታ ስለ ጽድቅ ብሎ መተው፣ መታገሥ ነው።

## <u>ክፍል 19፥</u>

## <u>መ</u> ጾም, ጸሎት ለምን ይጠቅማል?

## ከምንስ ያድናል?

<u>በልዩ ልዩ ቅዱሳት መጻሕፍት እንደምንመለከተው፥ ጾም ከቀደምት</u> አበው (አባቶች) ነቢያት ጀምሮ በየደረጃው፣ በየክፍሉ እየተጾመ መልካም ውጤት የታየበት ነው።

አዎ ጾም ጸሎት ብዙ ረድኤት የተገኘበት፣ ቅዱሳን፣ ጻድቃንና ሰማዕታት፤ እውነተኞች የእግዚአብሔር ወዳጆች ሁሉ የተጠቀሙበት ሀብተ መንፈስ ቅዱስም ነው።

<u>ለምሳሌም፥ <<ኢዩ 1፥13, 2፥12 መዝ 68፥10>> እንመልከት።</u>

<u>አዎ ጾም, ጸሎት ከሞተ ሥጋ፣ ከሞተ ነፍስ፥ ከፍዳ ከመርገም ከኃጢአትና ከመቅሰፍት ያድናል።</u>





<u>ጾም, ጸሎት፥ ከሐሰት ወደ እውነት፣ ከኃጢአት ወደ ጽድቅ ይመልሳል።</u>

<u>ጾም, ጸሎት፥ የመንግሥተ ሰማያትን መንገድ ያሳያል፣</u>

<u>ጾም, ጸሎት፥ የመንግሥተ ሰማያትን በር ያንኳኳል፣</u>

<u>ጾም,ጸሎት፥ በትክክለኛው መንገድ ወደ መንግሥተ ሰማያት ያስገባል።</u>

<u>ስለሆነም፥ ጾምን እንድንጾም፣ ጸሎትንም እንድናዘወትር (እንድንጸልይ) በብሉይ ኪዳንና በሐዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት ታዘናል።</u>

## <u>ክፍል 20፥</u>

## <u>ሠ</u> << ጾም በብሉይ ኪዳን>>

<u>1ኛ በትንቢተ ዮናስ ምዕራፍ 3፥5 እንደምንመለከተው</u> የነነዌ ሰዎች አመድ ነስንሰው፣ ድንጋይ ተንተርሰው፣ ማቅ ለብሰው እግዚአብሔርን በጾም፣ በጸሎትና በልቅሶ ስለ ለመኑ፣ ንጉሡም መሣፍንቱም፣ ትልቁም፣ ትንሹም፥ እንስሳትም ጭምር ለሦስት ቀን ያህል ምግባቸውን ተከልክለው በልዩ ሱባኤ ንስሓ ስለገቡ፥ በበደላቸውና በጥፋታቸው ተፀፅተው፥ ወደ እውነተኛው አምላካቸው ወደ ፈጣሪአቸው ወደ እግዚአሔር ስለ ጮኹ፤ እግዚአሔርም ጭኸታቸውን ሰማ፥ ልመናቸውንም ተቀበለ።

ሳይመክርና ሳያስጠነቅቅ የማይቀጣ የርኅራኄ አምላክ እግዚአሔር የፍጥረቱ ጥፋት ያሳዝነዋልና፣ የነነዌ ሰዎች በነቢዩ በዮናስ አማካይነት የተነገራቸውን ማስጠንቀቂያ ሰምተው ከጥፋት ጉዞአቸው ወደ እርሱ ወደ መሓሪው ፈጣሪአቸው ወደ እግዚአሔር ስለ ተመለሱ፥ እግዚአሔር ማራቸው።

አዎ እግዚአሔር ፍጥረቱ ሲጠፋ ቸል ስለማይል በተለይም በእንስሳትና ምንም በማያውቁ ሕፃናት መደምሰስ ስለአልጨከነ ይቅር ባይ እግዚአብሔር እንደበደላቸው ሳይሆን የነነዌን ሰዎች እንደቸርነቱና እንደ ምሕረቱ ይቅር አላቸው፥ ምሕረቱን ስለላከላቸውም በበደላቸው ምክንያት በላያቸው ላይ ታዞ ከነበረው መቅሰፍት ተረፉ፤ የእግዚአብሔር ቸርነት፣ ምሕረቱ፣ ይቅርታውና ርኅራኄውም በተግባር ላይ ታየማለት ነው። <u>ዮና 3፥5</u>

<u>2ኛ</u> ነቢያት 40,40 ቀን እየጾሙ ብዙ ተአምራት አድርገዋል። ይልቁንም የእግዚአብሔር ልዩ ወዳጅ የሆነው ሙሴ፥

<<40 ቀንና 40 ሌሊት ጾሞ፣ ጸልዮ>> በእግዚአብሔር እጅ የተጻፉት የኪዳን ቃላት (ቃል ኪዳን) ያለባቸውን ሁለት የድንጋይ ጽላቶች ከእግዚአብሔር ተቀብሏል ዘዳ 9፥9፥

ሊቁ ቅዱስ ያሬድም በድጓው <<ሃሌ ሃሌ ሉያ በጾም ወበጸሎት፣ ተመጠወ ሙሴ ኦሪተ>> አሥርቱ ቃላተ በማለት አመሥጥሮታል። (ሙሴ ኦሪትንና አሥር ቃላት ከእግዚአብሔር ተቀበለ ማለት ነው)

<<ዓሠርቱ ቃላት እለ ተጽሕፉ በአጻብዒሁ ለእግዚአብሔር>> (ዓሠርቱ,አሥር ቃላት በእግዚአብሔር እጅ የተጻፉት ናቸው ይላል የእሑድ ሰንበተ ክርስቲያን ውዳሴ ማርያምም)

እንደገናም <<40 ቀንና 40 ሌሊት ጾሞ፣ ጸልዮ>> በእግዚአብሔርፊት ወድቆ ፈጣሪውን በመለመን ይቅርታንና ምሕረትን ከእግዚአብሔር አማልዶ ሕዝበ እስራኤል በበደላቸው ምክንያት ተፈርዶባቸው ከነበረው የመቅሰፍት ቅጣት እንዲድኑ አድርጓል።

(ስለ ምልጃና አማላጅነትም ከዚሁ መገንዘብ እንችላለን) ዘዳ 9፥25

<<ሙሴ አሁንም (በቃለ ኪዳንና) በትእዛዝ (በርእሰ ሕግ) የታወቁትን አሥሩን ቃላት በሚቀበልበት ጊዜ <<40 ቀንና 40 ሌሊት እየጾመ እየጸለየ>> ከእግዚአብሔር ጋር ይገናኝ እንደ ነበር። በዘፀ ምዕራፍ 34፥27>> ተዘግቦ ይገኛል።

ሕዝበ እስራኤልም በግብጽ የግፍ አገዛዝ ሥር በነበሩበት ዘመን እግዚአብሔርን በጸሎትና በልቅሶ ስለ ለመኑ የጽድቅና የርኅራኄ ባለቤት ልዑል እግዚአብሔር ልቅሶአቸውን ሰማቸው፣ ልመናቸው ንምተቀበለ፣ በመልአከ ምክሩ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክትና የእርሱ ባለሟል፣ ታማኙና ወዳጁ በሆነ በሙሴ አማካይነት ከክፉ የባርነት ግዛት ነጻ አውጥቷቸዋል ዘፀ 2፥23።

ይኸውና ጾም, ጸሎት ከግፈኞች ያድናል፥ ከክፉው አገዛዝና ከጭቆናም ነጻ ያወጣል ማለት ነው።
ታዲያ ግን ጾም ሲባል ከዚህ ከፍ ብሎ እንደተገለጸው ከሥጋ ፍላጎት በመቆጠብ፣ ሥጋን ለፈጣሪው በማስገዛት፣ መንፈሳዊውን ሥራ በመሥራት ነው።

በመሆኑም ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት አስቀድሞ ሥጋን በጾምና በጸሎት ተቆጣጥሮ ለእግዚአብሔር ማስገዛት እንደሚገባ፣ ጠቃሚም እንደሆነ ለማስገንዘብ ነፍሴን በጾም አደከምኋት ብሎ በመዝ 34፥13፣





ጉልበቶቼ በጾም ደከሙ፣ ሥጋዬም ቅቤን በማጣት ከሳ ደረቀ ብሎም በመዝ 108፥24 ዘምሯል።

ነቢዩ ዳንኤልም በጾም ጊዜ ምርጥ ምርጥ ምግቦችንና የሚያሰክር መጠጥን መውሰድ (መጠቀም) እንደማይገባ፥ በቅቤና በመሳሰለው መለምለምም ተገቢ እንዳልሆነ ሲያስረዳ፥<<እኔ ዳንኤል ሦስት ሳምንት ሙሉ ሳዝን ነበር፣ ማለፊያውን እንጀራ አልበላሁም፣

ሥጋና ጠጅም በአፌ አልገባም፣ ሦስት ሳምንት እስኪፈጸም ድረስ ዘይትንም አልተቀባሁም>> ብሏል። ዳን 10፥2

አዎ እነዚህ የእግዚአብሔር ወዳጆች ሲሆኑ መላ ሕይወታቸውን ለፈጣሪያቸው ያስገዙ፥ በጾማቸውና በጸሎታቸው ብዙ ችግርን ያስወገዱ ብዙ ችግረኞችንም የረዱ ናቸው።

## ክፍል 21፥

## ረ <<ጾም በሐዲስ ኪዳን>>

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ጾም ለነፍስ ፍጹም መድኃኒት መሆኑን ለማረጋገጥ ገዳመ ቆሮንቶስ (ወደ ቆሮንቶስ በረኻ) ገብቶ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ጹሟል።

ይኸውም በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 4፥1 ጀምሮ በሰፊው ተዘግቦአል።

ሙሉውን ዝርዝር ወደ ፊት ከቦታው በገጽ 94 እንመለከተዋለን።

እንዲሁም ከዚህ ቀጥለው ያሉትን እንደ ምሳሌ ብንመለከት እኛም እንድንጾም ታዘናል።

ጽድቅን የሚራቡ (ስለ ጽድቅ ብለው የሚራቡና የሚጠሙ) ብፁዓን ናቸው ይጠግባሉና። ማቴ 5፥6።

የዚህንም ዝርዝር ወደ ፊት ከቦታው ገጽ 93። እናገኘዋለን።

በዚያን ጊዜም ከጾሙ፥ ከጸለዩም፣ እጃቸውንም ከጫኑ በኋላ አሰናበቱአቸው ይላል። የሐ ሥራ 13፥3።

ቅዱስ ጳውሎስም በዕብራውያን መልእክቱ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናትና፣ ዛሬ፣ እስከ ዘለዓለምም ያው ነው። <<ልዩ ልዩ ዓይነት በሆነ በእንግዳ ትምህርት አትወሰዱ>> ልባችሁ በጸጋ ቢጸና መልካም ነው እንጂ <<በመብል>> አይደለም፥ በዚህ የሚሠሩባት አልተጠቀሙምና በማለት በጾም ጊዜ ከመብል መቆጠብ እንደሚገባ ገልጾአል። ዕብራ 13፥9።

ስለሆነም ጾም በሕግ የተደነገገ ነው፣ ጾም በመመሪያ የተሰጠን ነው፥ ጾም ከእግዚአብሔር የታዘዘ ነው፣ ጾም የሥጋና የነፍስ መድኃኒት ነው።

## አዎ ጾም ጤና ነው፤

ጾም የነፍስ ደስታ ነው፣
ጾም ኃይል ነው፥

ጾም እውነተኛውን ሕይወት ያሰጣል፣
ጾም ድኅነትን (ሕይወትን) ያመጣል፣
ጾም ትዕግሥትን ያስይዛል፤

ጾም ርኅራኄን፣ ትሕትናንና ፍቅርን ያስተምራል፣
ጾም የጽድቅን መንገድ ይመራል፤

ጾም ወደ እግዚአብሔር ያቀርባል፣
ጾም ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወት፣ ወደ መንግሥተ ሰማያት ይወስዳል።

በመሆኑም ይህን ለማግኘት ሁላችንም መጾም፣ መጸለይ ይገባናል ማለት ነው።

## ክፍል 22፥

ሰ ከዚህ ቀጥለን በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ሃይማኖታዊ ቀኖና ታውቀው እንዲጾሙ የተመደቡትን የአጽዋማት ቊጥርንና ስማቸውን በዐጭሩ በመዘርዘር እነማን በጾም በጸሎት ድነዋል? እነማንስ በጾም በጸሎት ተጠቅመዋል? እያልን በጥያቄ መልክ እያነሣን መልሶቻቸውን ከነማስረጃቸው እንመለከታለን።





በሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ባህልና ሃይማኖታዊ ትውፊት (ቅብብሎሽ) ውስጥ ያሉት አብያተ ክርስቲያናት የሐዋርያትን የጾም ሕግ መነሻ በማድረግ የሚጾሙት የጾም ሥርዓት እንዳላቸው ይታወቃል።

በተለይም ደግሞ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ከጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት መካከል የመጀመሪያይቱ፣ አንደኛ ዋናዋ እንደመሆኗ መጠን፥ በቊጥር የታወቁና ስማቸው የተገለጸ፥ በሃይማኖታዊ የጾም ሥርዓት (በሥርዓተ ቀኖና) ተወስነው እንዲጾሙ የተመደቡ ሰባት አጽዋማት እንዳሏት ግልጽ ነው።

እንደዚሁም የሐዋርያትን የጾም ሕግ መሠረት በማድረግ የምታከናውነው በፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ 15 የተደነገገ ሥርዓተ ጾም (የጾም አፈጻጸም) አላት።

እነዚህ ሁሉ በየደረጃው የሚገለጹ ሲሆኑ፥ መጀመሪያ ግን የሰባቱ አጽዋማት ዝርዝርንና ምሥጢራቸውን እንመለከታለን።

## በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ሃይማኖታዊ ቀኖና ፍ.መ.አ. 15 እንዲጾሙ የተመደቡት አጽዋማት ቊጥርና የስማቸው ዝርዝር፥

### 1ኛ የነነዌ ጾም፥

ጾመ ነነዌ (የነነዌ ጾም) በጥር (በየካቲት) ወር በዓመት ሦስት ቀን ብቻ ሰኞ፣ ማክሠኞና ሮብ የሚጾም ነው።

ቀኑ በባሕረ ሐሳብ ስለሚወጣ በየዓመቱ ሊቀያየር ይችላል። (ትንቢተ ዮናስ 1፥1 ጀምሮ)

ሙሉ ዝርዝሩ ከቦታው ገጽ 66 ስለ አለ ከዚያው እንመልከት፥

### 2ኛ ጾመ ነቢያት (የነቢያት ጾም)

ይህ ጾም፥ በየዓመቱ ከኅዳር 15 ቀን እስከ ታኅሣሥ 28 ቀን የሚጾም ነው። ነገር ግን በዘመነ ዮሐንስ የጳጕሜን ወር 6 ቀን ስለሚሆን ልደት ታኅሣሥ 28 ቀን ይከበራልና፥ ከኅዳር 14 ቀን እስከ ታኅሣሥ 27 ቀን ድረስ ይጾማል ማለት ነው።

ጾሙ ነቢያት የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መምጣትንና መወለድን በጕጕት እየተጠባበቁ ስለ ሥጋዌው (ስለ ልደቱ) የጾሙት ነው።

## 3ኛ ዐቢይ ጾም (የጌታችን ጾም ነው)

የዐቢይ ጾም (የጌታችን ጾም) ጠቅላላ ዝርዝርና መሠረታዊ ምሥጢሩ ሁሉ በሰፊው በቦታው በጾሙ ክፍል ገጽ 94 ስለ ተጻፈ ከዚያው እንመልከት (ማቴ 4፥1 ጀምሮ)

## 4ኛ ጾመ ሐዋርያት (የሰኔ ጾም)

የሰኔ ጾም፥ ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ ወንጌልን ለማስተማር አስቀድመው የጾሙት፤ የተልዕኮኣቸው መሠረት ያደረጉበት፥ የማስተማርና ድውያንን የመፈወስ ሥራቸው ሁሉ የተቃና እንዲሆንላቸው ፈጣሪኣቸውን በጾምና በጸሎት የለመኑበት ጾም ነው።

## 5ኛ የፍልሰታ ጾም (የእመቤታችን ጾም)

ይህ የፍልሰታ ጾም በመባል የሚታወቀው የእመቤታችን ጾም ሁል ጊዜ ከነሐሴ 1 ቀን እስከ ነሐሴ 15 ቀን ድረስ ለ15 ቀናት ብቻ የሚጾም ሐዋርያት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ለማየትና ለማግኘት የጾሙት ነው።

## 6ኛ ጾመ ገሃድ፥

ገሃድ ማለት መገለጥ፤ ግልጽነት ማለት ሲሆን፥ የጌታችን መወለድንና በግልጽ መታየትን ያመለክታል።

የገሃድ ጾም ልደትና ጥምቀት ዓርብ ወይም ሮብ ሲውሉ ስለ ማንጾማቸው ተውላጣቸው (የእነእርሱ ለውጥ ነው)

ይህ ጾም ሁል ጊዜ በልደትና በጥምቀት ዋዜማ ለ1 ቀን ብቻ እስከ ምሽቱ ድረስ ይጾማል። ዋዜማው ቅዳሜና እሑድ በሚሆንበት ጊዜም እስከ ማታ አንጾምም እንጂ በፍስክ ቀን የሚበሉትን እንደ ሥጋ፤ ቅቤ፤ ወተትና እንቍላል የመሳሰሉትን አንበላም ማለት ነው።





## 7ኛ ዓርብና ሮብ ናቸው።

ሮብ፥ አይሁድ ጌታችንን ለመያዝ የመከሩበትና ምክራቸው የተሳከበት፤ ምክረ መስቀል (ምክረ ሞት) የተፈጸመበት ሲሆን፥ ዓርብም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት በመሆኑ የሮብና የዓርብ ጾም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ሲል የተቀበለውን ልዩ ልዩ መከራ በማስታወስ ነው የምንጾመው።

የእነዚህ ምሥጢር ሁሉ በእየቦታው በሰፊው ተገልጿል። በሚገባም ተብራርቷልና ከዚያው እንመልከት። በተለይም ምዕራፍ 11 ገጽ 127 እና ከሰሙነ ሕማማት ውስጥ ይገኛል።

## ክፍል 23፥

## ዐቢይ ጾም፥

## ሀ ዐቢይ ጾም ማለት ምን ማለት ነው?

የጾም ጥሬ ንባብና ትርጉሙ ከላይ እንደተገለጸው ሲሆን፥ ዐቢይ ደግሞ፥ <<ዐብየ ከፍ ከፍ አለ ትልቅ ሆነ>> ይልና ዐቢይ ትልቅ ብሎ ይገኛል።

ስለሆነም ዐቢይ ጾም ስንል ትልቅ ጾም ማለታችን ነው።

ትልቅ ጾም ወይም ዐቢይ ጾም መባሉም፥

1ኛ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ጾመው፥

2ኛ በቁጥር ወይም በዕለታት ብዛት ከሌሎች አጽዋማት የሚበልጥ በመሆኑና በፍጥረቱ ሁል ጊዜ <<ዐቢይ እግዚአብሔር ወብዙኀ ኃይሉ>> እግዚአብሔር ትልቅ ነው፤ ገናናም ነው።

ምስጋነውም ብዙ ነው፤ ፍጹምም ነው እየታባለ የሚመሰገን የአምላካችን፤ የፈጣሪኣችን ጾም ስለ ሆነ ነው። መዝ 47፥1።

## <<ጾመ ሁዳዴ>>

ጾመ ሁዳዴ ስንልስ ምን ማለታችን ነው?

ሁዳዴ ማለት ደግሞ የመንግሥት፣ የሀብታም (የብዙ ሕዝብ) ሰፊ እርሻ ማለት ሲሆን፥ ዐቢይ ጾምም ጌታችን የጾመው፣ ሁሉም ሕዝበ ክርስቲያን የሚጾመው ትልቅ ጾም ስለ ሆነ በሁዳዴ ይመሰላል፣ በሁዳዴ ስም ይጠራል ማለት ነው።

## ክፍል 24፥

## <<ዘወረደ>>

### ቀ ዘወረደ ማለት ምን ማለት ነው?

የመጀመሪያ ጾም መግቢያ ሰንበት ወይም እሑድ ዘወረደ ይባላል።

ከጌታችን ጾም አስቀድሞ የሚገኘው ዘወረደ የሚባለው እሑድና ሳምንቱ የዐቢይ ጾም መጀመሪያ (ዋዜማ) ሲሆን፥ ለዋናው የጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጾም መቅድሙ (መግቢያው) ነው።

ዘወረደ መባሉም በቅዱሳት መጻሕፍት በየክፍሉ ተዘግቦ እንደምናገኘው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ፣ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ዓለምን በማዳኑ፥ ወረደ መጣ ስለተባለ በጌታችን ከሰማይ መውረድ ምክንያት፣ ወደዚህ ዓለም በመምጣቱ ምሥጢር ነው።

ሊቁ ኢትዮጵያዊ ቅዱስ ያሬድም በግእዙ <<ዘወረደ እምላዕሉ አይሁድ ሰቀሉ>>

ትርጉሙ፥ ከላይ (ከሰማይ) የወረደውን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አይሁድ ሰቀሉት በማለት በጣዕመ ዜማው አመሥጥሮታል። (ከጾመ ድጓው መጀመሪያው ላይ ይገኛል)።





ስለዚህም ዘወረደ የጌታችን ሥጋዌ (ሰው መሆን) መታሰቢያ ነው ማለት ነው።

በተጨማሪም፥<<ማቴ 1፥23, 2፥1, ሉቃ 1፥26, ዮሐ 1፥1, 3፥12>> እንመልከት።

## ክፍል 25፥

## <<የዘወረደ ጾም>>

### በ የዘወረደ ጾምስ ምንድ ነው?

ዘወረደ የዐቢይ ጾም መጀመሪያ ሳምንት ሲሆን፥ ጾሙም ጾመ ሕርቃል ይባላል።

## << ጾመ ሕርቃል መባሉ>>

በአንዳንድ የአባቶች ጉባኤ እንደሚተረከው ፎቃ የተባለ አይሁዳዊ ንጉሥ በኢየሩሳሌም በሚኖሩት ክርስቲያኖች ላይ የግፍ አገዛዙን አጽንቶ ስለ አስቸገራቸው ክርስቲያኖቹ በወቅቱ ኃይለኛ ገዥ ለነበረው ሕርቃል ለተባለው የሮም ንጉሥ፥ የቢዛንታይን ንጉሥ ነውም ይባላል።

ያም ሆነ ይህ እባክህ ፎቃን አስወግደህ ከዚህ ክፉ አገዛዝ ገላግለን ብለው ቢልኩበት ሕርቃል ሐዋርያት በሲኖዶሳቸው ሰውን የገደለ ዕድሜ ልኩን ይጹም ብለው ሥርዓት ሠርተዋልና አይሆንም ስለአላቸው ክርስቲያኖቹ ይህን ክፉ ገዥ አጥፋልን እንጂ ጾሙንስ ተካፍለን እንጾምልሃለን እንዳሉትና ሕርቃልም እንግዲያስ እሺ ብሎ ተስማምቶ ፎቃን በማጥፋት ክርስቲያኖችን ከችግርና ከክፉ አገዛዝ ስለገላገላቸው አንድ ላይ እንደጾሙትና በዚህ ምክንያት ጾመ ሕርቃል እየተባለ እንደሚጠራ ይታወቃል።

ይህ ጾም ቀደምት አባቶቻችንና የቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት ሁሉ ስለጾሙት ከጌታችን ጾም ተጨምሮ በዐቢይ ጾሙ መግቢያ ሳምንት እንዲጾም በፍትሐ መንፈሳዊ አንቀጽ 15 ተደንግጓል።

ስለሆነም ሕዝበ ክርስቲያን ሁሉ እየጾመው ይገኛል።

የዘወረደ ቃለ እግዚአብሔር በሙሉ፥ ከአሁን ቀደም ለሥጋችሁ የተገዛችሁበት፥ በሥጋችሁ የተደሰታችሁበት ጊዜ ይበቃል።

ከእንግዲህስ በኋላ ጹሙ፣ ጸልዩ፣ ለነፍሳችሁ አስቡ፥ ለእግዚአብሔር ተገዙ ይለናል። ማር 14፥38።

ቅዱስ ጳውሎስም በገላትያ ምዕራፍ 5፥16 መልእክቱ፥ <<ነገር ግን እላለሁ በመንፈስ ተመላለሱ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ፥ ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ ስለዚህም የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም>> በማለት አስተምሮናል።

መልእክቱ የሥጋን ፍላጎት ብቻ ተከትለን የምንጓዝ ከሆነ ከቅዱስ መንፈስ ውጭ ስለምንወጣ ፍጹም የሆነውን ሕይወት ማግኘት እንደማንችል ነው የሚያስገነዝበን።

በተጨማሪም ከዚህ በታች ያሉትን ጥቅሶች እንመልከታቸው።

1ኛ ለእግዚአብሔር <<በፍርሃት ተገዙ>> ዋጋ ያለበት ነውና በረዓድም ደስ ይበላችሁ። መዝ 2፥11።
(ሕጉንና መመሪያውን እየጠበቃችሁ ትእዛዛቱንም እየፈጸማችሁ ኑሩ ማለት ነው)።

2ኛ በሌሊት በቤተ መቅደስ እጆቻችሁን አንሡ እግዚአብሔርንም ባርኩ። መዝ 133፥2

3ኛ ስትጸልዩ ወገባችሁ የታጠቀ፣ መብራቶቻችሁም የበራ ይሁን። ሉቃ 12፥35

4ኛ ወንድሞች ሆይ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው፥ ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ። ሮሜ 12፥1

5ኛ ይልቁን አሁን በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ። ፊል 2፥12

6ኛ ፍቅራችሁ ያለ ግብዝነት ይሁን፣ ክፉውን ነገር ተጸየፉት፣ ከበጎ ነገር ጋር ተባበሩ። ሮሜ 12፥9





7ኛ በተቀደሰ አሳሳም (ሰላምታ) እርስ በእርሳችሁ ሰላምታ ተሰጣጡ (ሰላም ተባባሉ) ሮሜ 16፥16

8ኛ በፍቅር አሳሳም እርስ በእርሳችሁ ሰላምታ ተሰጣጡ፥

በክርስቶስ ላላችሁ ለሁላችሁ ሰላም ይሁን። 1ኛ ጴጥ 5፥14።

(በእውነተኛው ፍቅር ተስማሙ ከልብ ሰላም ተባባሉ ማለቱ ነው)

9ኛ በትሕትና፣ በየዋህነትና በትዕግሥት እርስ በእርሳችሁ በፍቅር ታገሡ (ተፋቀሩ) ኤፌ 4፥2

10ኛ እውነትን ተነጋገሩ፣ ኃጢአትንም አታድርጉ፣ በቍጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ፣ ለዲያብሎስ ፈንታን አትስጡት።

(ተሉ ታረቁ ማለቱ ነው)

እርስ በእርሳችሁ ቸሮችና ርኅሩኆች ሁኑ፣ እግዚአብሔር ደግሞ በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ ይቅር ተባባሉ።

ኤፌ 4፥ ቍጥር 26 እና ቍጥር 32 እንመልከት።

11 እንግዲህ እንደ ባለ አእምሮ አስቡ፣ ትጸልዩም ዘንድ በመጠን ኑሩ፥ ፍቅር የኃጢአትን ብዛት ይሸፍናልና ከሁሉ በፊት እርስ በእርሳችሁ አጥብቃችሁ ተፋቀሩ። 1ኛ ጴጥ 4፥8

12 እንግዲህስ ለእግዚአብሔር ተገዙ፣ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙት፣ ከእናንተም ይሸሻል፥ ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል። ያዕቆብ 4፥7

አዎ ይህ ቅዱስ ቃል በትሕትና፣ በንጽሕና እና በእውነተኛው ፍቅር አንድ በመሆን እየተረዳዳን እንድንኖር፥

እየጾምን፣ እየጸለይን፣ በፍጹም ልባችን ወደ ፈጣሪያችን ወደ እግዚአብሔር እንድንቀርብ ነው እየመከረን ያለ።

እነዚህ ጥቅሶች ለአስፈላጊው ማብራሪያ እየተደረገበት ከልዩ ልዩ ክፍል የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ናቸው።

## ክፍል 26፥

## ተ ዐቢይ ጾም፥ ለመሆኑ ጾም እስከ ስንት ሰዓት ነው የሚጾመው?

በአጠቃላይ ሁሉም ጾም እስከ ቀኑ 9 ሰዓት (3 p.m) ነው የሚጾም።

ነገር ግን አንድ አንድ አጽዋማት ከ9 ሰዓት በላይ እንዲጾሙ የሚያደርግ የየራሳቸው የሆነ ምሥጢር አላቸው።
በዚሁም መሠረት ዐቢይ ጾም ከትንሣኤ በኋላ ኀምሳ ቀን ሮብና ዓርብ የማንጾምበት ምክንያት፥ ሰፋ ያለ ምሥጢር ስለ አለበት ከ9 ሰዓት (3 p.m) በላይ እንዲጾም ተወስኖአል።
ይኸውም ትርፍ ሰዓቱ በበዐለ ኀምሳ ለማይጾሙ ሮብና ዓርብ የሚካፈል እንደሆነ ይነገራል። ትርፍ ሰዓቱ በበዓለ ኀምሳ ለማንጾማቸው ሮብና ዓርብ ሲካፈል 9, 9 ሰዓት ይደርሳቸዋል ማለት ነው።

(ይህ ከአበው የጉባኤ መምህራን፣ በተለይም ከቃል ትምህርት የተገኘ ምሥጢር ነው)።

ነገር ግን በበዐለ ኀምሳ የሚገኙ ሮብና ዓርብ አለመጾማቸው በመንግሥተ ሰማያት ጾም፣ ረኀብ እንደሌለ የሚያመለክት መሆኑ ደግሞ በሊቃውተ ቤተ ክርስቲያን በሌላ መልኩ ይገለጻል።

ስለዚህም ከቅዳሜና ከእሑድ በስተቀር የመጀመሪያ ጾም የዘወረደ ሳምንት፥ እስከ ቀኑ 12 ሰዓት (6 p.m)

ከቅድስት እስከ ሆሳዕና ያሉት ሳምንታት እስከ ቀኑ 11 ሰዓት (5 p.m) ድረስ

ሰሙነ ሕማማትም እስከ ምሽቱ 1 ሰዓት (7 p.m) ድረስ እንዲጾም በፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ 15 ተወስኖአል።

ይህን ያህል ሰዓት ማን ይጾማል የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል።

አዎ እንደሚከብድ ይገመታል ቢሆንም በሥርዓተ ቀኖናው ታዟል።





ይህን ጾም በተለይም በገዳም ያሉት አባቶችና ባሕታውያን፥ እንዲሁም ለዚህ የታደሉ ወገኖች ይጾሙታል ይላሉ አባቶቻችን በጉባኤ ትርጓሜያቸው።

ሌሎቻችን ለዚህ ያልታደልን በሥራና በተለያየ ምክንያት እስከ ተባለው ሰዓት መቆየት ባንችልም እንኳ እስከ ቀኑ 9 ሰዓት (3 p.m ) ግን መጾም ይገባናል።

ምክንያቱም ሃይማኖታዊ ግዴታ ነው መጽሐፋዊ ትእዛዝም ነው።

## ጾምን እንዲጾሙ የማይገደዱ፥

>>> ዕድሜያቸው ከ7 ዓመት በታች የሆኑት ልጆች፥
>>> ለመዳን ተስፋ ያላቸው በከባድ ችግር ላይ ያሉት ሕሙማን፥ እና ጉዳት የደረሰባት (በወሊድ የተዳከመች) አራስ ብቻ ናቸው። ከዚህ በተረፈ ግን ሁሉም ሕዝበ ክርስቲያን እንዲጾም በቤተ ክርስቲያናችን የጾም ሥርዓት ታዟል።

በመሆኑም፥ እኛ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትንና ሥርዓትን የምንከተል ሁላችንም ጌታችንን፥ ሐዋርያትን ቀዳማውያን ቅዱሳን አባቶቻችንንና የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንትን አብነት በማድረግ በየዓመቱ በዐዋጅ የምንጾመው፥

ዐቢይ ጾም በመባል የሚታወቀው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጾም፥ ሁል ጊዜ በባሕረ ሐሳብ ስለሚወጣ በየጊዜው ወሩ ሊቀያየር ቢችልም የመጀመሪያው ቀኑ ግን ዘወትር ሰኞ ስለሚሆን ዐቢይ ጾሙን እንደተለመደው በሥርዓተ ቀኖናችን መሠረት እንድንጾመው ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን መልእክቷን በዐዋጅ ታስተላልፋለች ማለት ነው።

ዐቢይ ጾም ያለፈው ለሥጋችሁ የተገዛችሁበት ጊዜ ይበቃችኋል ከእንግዲህ ወዲህስ ጹሙ፣ ጸልዩ በተባልነው መሠረት፥

እየጾምን፣ እየጸለይን፥ ነፍሳችንን በመንፈስ ቅዱስ የምናስደስትበት፣ ሰውነታችንን ለእግዚአብሔር የምናስገዛበት፣ የጽድቅ ሥራን የምንሠራበት፥ ልዩ የሆነ የሕይወት ወቅት ነው።

(በተጨማሪም መዝ 2፥11, ፊል 2፥12, ዕብራ 12፥28, እና 1ኛ ጴጥ 1፥17 እንመልከት)